**ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ**
**ኢየሱስ ክርስቶስ**
**ካህኑ ለዓለም፡ በከመ ሢመቱ ለመልከ ጼዴቅ ኢትዮጵያዊ**
**ንጉሠ ጽዮን፥ ወንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ**

**The Conquering Lion of the Tribe of Judah**
**Jesus Christ**
**Eternal Priest in the Order of Melche-Zedeq the Ethiopian**
**King of Zion and King of Kings of Ethiopia**

**ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር**
**ድንግል ማርያም**
**እሙ ለአምላክነ፥ ወእምነ ዘዚአነ**
**ንግሥተ ጽዮን፥ ወንግሥተ ነገሥታት ዘኢትዮጵያ**

**Ethiopia stretches out Her Hands to God**
**The Virgin Mary**
**Mother of God and Our Holy Mother**
**Queen of Zion and Ethiopia**

**ቍጥር ፩/፳፻፫ ዓ. ም.**

# ቃለ ዐዋዲ!

## እምኢትዮጵያ፡ ዘመንግሥተ እግዚአብሔር።

# የአዋጅ ቃል!

## ከኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት።

በስመ እግዚአብሔር አብ፥ ወወልድ፥ ወመንፈስ ቅዱስ፤
አሓዱ አምላክ፤ በቅድስት ሥላሴ፤

በስመ እግዝእትነ፥ ወእምነ፥ ወሃይማኖትነ፥ ወሀገሪትነ፥
ወንግሥትነ፡ ቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ፤

በኃይለ መስቀሉ፡ ዘእግዚእነ፥ ወአቡነ፥ ወመድኃኒነ፥
ወካህንነ፥ ወንጉሥነ ኢየሱስ ክርስቶስ፡
ወልደ-እግዚአብሔር ሕያው፥ ወወልደ ማርያም ሥግው።

ማለትም፦

በልዩ ሦስትነት፡ አንድ አምላክ በኾነው፡
በእግዚአብሔር አብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ ስም፤

እናታችንና ሃይማኖታችን፥ አገራችንና ንግሥታችን
በኾነችው፡ አምላክን በወለደችው፡
በእመቤታችን፡ ቅድስት ድንግል ማርያም ስም፤

በአምላክነቱ፡ የእግዚአብሔር ልጅ፥
በሰውነቱም፡ የማርያም ልጅ በኾነው፡
አባታችንና መድኃኒታችን፥ ካህናችንና ንጉሣችን
ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በመስቀሉ ኃይል።

\+ + +

# መቅድም።

የእግዚአብሔር መንግሥት የኾነችው፡ የኢትዮጵያ፡ ልጆቿና ነጋሢዎቿ፥ ካህናቷና ዜጎቿ ኾናችሁ፡ በእግዚአብሔር ሕይወት የምትኖሩት፡ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ ለሰማዩ አባታችሁ: ለልዑል እግዚአብሔር እና ለሰማዩቷ እናታችሁ፡ ለድንግል ማርያም፡ ዘወትር የምታቀርቧቸውን፡ ከዚህ በታች የሠፈሩትን የሃይማኖትና የቅዱሱ ኪዳን፥ እንዲሁም፡ የምስጋናና የሰላምታ ጸሎቶቻችሁን ሕያዋን ቃላት፥ ደግሞም፡ ለዚህ፡ ለታላቁ ቃለ ዓዋዲ፡ ቀዳሚ መግለጫ ኾኖ የተላለፈውን ሰፊ መልእክት፡ መሠረትና ዐባሪ በማድረግ፡ ይህ የአዋጅ ቃል፡ ለፍጥረተ-ዓለሙ ኹሉ፡ በይፋ እንዲነገርና እንዲታወቅ፡

## ከኢትዮጵያ የእግዚአብሔር መንግሥት ታውጇል።

፩ኛ. ነአምን፡ በአሐዱ አምላክ፡ እግዚአብሔር አብ፡ አኀዜ ኵሉ፤ ገባሬ ሰማያት ወምድር፣ ዘያስተርኢ፥ ወዘኢያስተርኢ።

ወነአምን፡ በእግዚአብሔር ወልድ፡ አሐዱ እግዚእ፣ ወልደ አብ ዋሕድ፣ ዘህልው ምስሌሁ፡ እምቅድመ ይትፈጠር ዓለም፤ ውእቱ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ ብርሃን፡ ዘእምብርሃን፣ አምላክ፡ ዘእምአምላክ ዘበአማን፤ ዘተወልደ፤ ወአኮ ዘተገብረ፤ ዘዕሩይ ምስለ አብ፡ በመለኮቱ፤ ዘቦቱ ኵሉ ኮነ፤ ወዘእንበሌሁሰ፡ አልቦ ዘኮነ፣ ወኢምንትኒ፡ ዘበሰማይኒ፥ ወዘበምድርኒ።

ዘበእንቲአነ ለሰብእ፣ ወበእንተ መድኃኒትነ፡ ወረደ እምሰማያት፤ ተሰብአ፤ ወተሠገወ፡ በግብረ መንፈስ ቅዱስ፣ እማርያም፡ እምቅድስት ድንግል፣ በነሢአ ሥጋ፡ እምሥጋሃ፥ ወነፍስ፡ እምነፍሳ፡ ኮነ ብእሴ ፍጹመ። በመዋዕለ ጲላጦስ ጴንጤናዊ፡ ተሰቅለ፤ ወሐመ፤ ወሞተ፤ ወተቀብረ፡ በእንቲአነ፣ ወተንሥአ እሙታን፣ አመ ሣልስት ዕለት።

ዐርገ በስብሓት፡ ውስተ ሰማያት። ወነበረ፡ በየማነ አቡሁ፣ በመንበሩ ዘበዕሪና።

ዳግመ፡ ይመጽእ በስብሓት፤ ይኰንን፡ ሕያዋነ፥ ወሙታነ። ወአልቦ ማኅለቅት ለመንግሥቱ።

ወነአምን፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ። ውእቱ፡ መንፈሰ ጽድቅ፤ ማኅየዊ ዘበአማን፤ ዘሠረፀ እምአብ፣ ዘንሰግድ ሎቱ፣ ወንሰብሖ፡ ምስለ አብ፥ ወወልድ፣ ወዘነበበ በነቢያት፤ ዘወረደ ላዕለ ሐዋርያት፤ ወጸጋሁ ዘመልዓ ዓለመ፡ በቤዛ መስቀሉ፡ ለኢየሱስ ክርስቶስ።

ወነአምን፡ በአሓቲ ቅድስት ኢትዮጵያ፡ መንግሥተ እግዚአብሔር፡ እንተ ይእቲ ዘመሠረታ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ እምጥንት፥ በኪዳነ ልቦና፡ ዘሰብኣውያን ቀደምት፤ ወዘአጽንዓት፡ በቃለ ነቢያት፤ ወዘፈጸማ፡ በላዕለ ኵሉ ጉባኤ፡ ዘሐዋርያት። በውስቴታ፡ ያቄርቡ ካህናት፡ መሥዋዕተ ሥጋሁ ቅዱሰ፥ ወደሞ ክቡረ፡ ለኢየሱስ ክርስቶስ። ወባቲ ይትዌከፉ ምእመናን፥ ወምእመናት፡ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ፡ ዘዘዚአሁ።

ወነአምን፡ በአሓቲ ጥምቀት፡ ለሥርየተ ኃጢአት።

ወነአምን፡ በትንሣኤ ሙታን፤ ወሕይወተ ዘለዓለም፤ ለዓለመ ዓለም፤ አሜን።

ማለትም፡

ኹሉን በያዘ፣ ሰማይንና ምድርን፥ የሚታየውንና የማይታየውን በፈጠረ፡ አንድ አምላክ በሚኾን፡ በእግዚአብሔር አብ እናምናለን።

ዓለም ሳይፈጠር፡ ከእርሱ ጋራ በነበረ፥ አንድ የአብ ልጅ፥ አንድ ጌታ በሚኾን፡ በእግዚአብሔር ወልድም እናምናለን። እርሱም፡ ከብርሃን የተገኘ ብርሃን፥ ከእውነተኛ አምላክ የተገኘ አምላክ፥ የተወለደ እንጂ፡ ያልተፈጠረ፣ በመለኮቱ፡ ከአብ ጋራ የሚተካከል፣ ኹሉ፡ በእርሱ የኾነው፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። በሰማይ ካለው፣ በምድርም ካለው፡ ያለእርሱ፡ ምንም ምን፡ የኾነ የለም።

ስለእኛ ስለሰዎች፥ እኛን ለማዳን፡ ከሰማይ ወረደ፤ በመንፈስ ቅዱስ ግብር፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም፡ ከሥጋዋ፡ ሥጋ፥ ከነፍሷ፡ ነፍስ ነሥቶ፡ ፍጹም ሰው ኾነ። በጴንጤናዊው ጲላጦስ ዘመን፡ ስለእኛ፡ መከራን ተቀበለ። ተሰቀለ። ሞተ። ተቀበረ። በሦስተኛውም ቀን፡ ከሙታን ተለይቶ ተነሣ። በክብር፥ በምስጋና፡ ወደሰማይ ዐረገ። በአባቱም ቀኝ፡ በዙፋኑ ተቀመጠ። ዳግመኛም፡ በሕያዋንና በሙታን ለመፍረድ፡ በምስጋና ይመለሳል። ለመንግሥቱ፡ ፍጻሜ የለውም።

በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም እናምናለን። እርሱም፡ ሕይወትን የሚሰጥ፣ ከአብ የሠረፀና በነቢያት ዐድሮ የተናገረው፥ በሐዋርያት ላይ የወረደውና በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት፡ ዓለሙን፡ በጸጋው የሞላው፡ ቅዱሱ የእውነት መንፈስ ነው። ለእርሱም፡ ከአብና ከወልድ ጋራ፡ በአንድነት እንሰግድለታለን፤ እናመሰግነዋለንም።

ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ጥንት፡ በቀደሙት ሰዎች ኪዳነ ልቦና በመሠረታት፥ በነቢያት ቃል ባጸናትና በሐዋርያት ጉባኤ በፈጸማት፥ ካህናት፡ የእርሱን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም፡ ለመሥዋዕትነት በሚያቀርቡባት፥ ምእመናንና ምእመናትም፡ የመንፈስ ቅዱስን ጸጋዎች በሚቀበሉባት፡ በአንዲት ቅድስት ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት እናምናለን።

ኃጢአት በሚሠረይባት፡ በአንዲት ጥምቀት እናምናለን።

በሙታን ትንሣኤ፥ በዘለዓለምም ሕይወት እናምናለን። ለዘለዓለሙ፤ አሜን።

፪ኛ፡ ነአምን፡ በኢትዮጵያውናን፡ ዘኪዳን ቅዱስ፣ ህልው በዓቂበ ቃላት ኪዳናውያት፥ እለ ወሀቦን እግዚአብሔር፡ ለውሉደ ሰብእ።

አምላክነ፡ ሣረረ፡ ዝንቱ ሰብእና ኢትዮጵያዊ፡ በኪዳነ ልቦና፡ በዘኮነ፡ እምሥርዓተ ሰብሳብ፡ ዘአዳም ወሔዋን፡ በዘመነ ፍጥረት ቀዳማዊ፤ ወመትሎሁ፡ አዕረጎ ለዝ ሕንፃ፡ በቀስተ ደመናሁ፡ ለኖኅ፥ ወበቍርባኑ፡ ዘመልከ ጼዴቅ፥ ወበግዝረቱ፡ ዘአብርሃም፤ ወበዘመነ ሕግ ማእከላይ፡ ነደቆ ማኅፈዱ፡ በጽላተ ሙሴ፥ ወበመንበረ ዳዊት፡ ዘግህደ፡ በፅምረተ አሥራወ ዘርያሙ ለንግሥት ማክዳ ኢትዮጵያዊት፥ ወለንጉሥ ሰሎሞን እስራኤላዊ፡ ከመ ያስተሰነአዎ ኵለንታሁ፡ በኪዳነ ኦሪት። ወእምድኅረ አጽንዖቱሰ፡ በሥጋሁ ወደሙ፡ ለኢየሱስ ክርስቶስ፡ ወልዱ፡ ዘተወልደ እምድንግል ማርያም፡ እንተ ሠረፀት እምዛቲ ሥርው ምልዕት፡ አስተቄጸሎ አክሊል ዘለዓለም፡ በፍጻሜ ዘመን ዘሕይወት፡ በኪዳነ መንፈስ ቅዱስ።

በእንተዝ፡ ነአምን፡ ከመ ይእቲ ኢትዮጵያ፡ መንግሥተ እግዚአብሔር፡ እንተ ገዝፈት በሰብእናሁ ለኢትዮጵያዊ፡ ዘኪዳን ቅዱስ፡ እንዘ በኅቤሁ የኀብሩ፡ ቤተ ሕዝባ፥ ወቤተ ክህነታ፥ ወቤተ ምልክናሃ፡ በአሠረ ተዋሕዶ።

ንሕነ፡ እለ ተሰየምነ "ክርስቲያን"፡ በስመ ዚአሁ፡ ዘተብህለ፡ "ክርስቶስ"፡ ነአምን፡ ከመ ውእቱ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ካህንነ፥ ወንጉሥነ ዘለዓለም፡ በሢመቱ፡ ለመልከ ጼዴቅ ኢትዮጵያዊ፡ ዘአስተርአየ በመዋዕል ቀዳማዊ፡ ወዘኮነ አርአያሁ ለኢየሱስ ክርስቶስ፡ በልደቱ፡ ዘኮነ፡ እምትሥልስተ ዘርዕ፡ ዘእምአንጋደ ሴም፥ ወካም፥ ወያፌት።

ንሕነ፡ እለ ተሰየምነ፡ "ኢትዮጵያውያን ወኢትዮጵያውያት"፡ በስመ ዚአሃ፡ ዘተብህለት "ኢትዮጵያ"፡ ነአምን፡ ከመ ይእቲ፡ ድንግል ማርያም፡ ዕፀ ሕይወት፥ ወእመ ሕያዋን አማናዊት፥ ወታቦተ ጽዮን ዘለዓለማዊት፥ ወንግሥተ ሰማያት፥ ወምድር፡ በዘወሊዶታ ለአምላክ።

ነአምን፡ በቀስተ ደመና፡ ዘተሠርገወ፡ በሠለስቱ ዓበይት ኅብረ ቀለማት፡ ዘውእቶን፡ ሐመልሚለ፥ ወወርቀ፥ ወቀይሐ፡ ዘተውህበ ለነ፡ እምእግዚአብሔር፡ እንተ በኀበ ኖኅ፡ ከመ ውእቱ ይኩነነ፡ ትእምርተ ኪዳን፡ ዘለዓለም።

ነአምን፡ በማኅተምነ ዘለዓለም፡ ዘረከብነ እምአምላክነ፡ ወበዘውእቱ ዘተነግረ፡ በእንተ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ መፈጽም፡ ለኪዳኑ ቅዱስ፡ በዝንቱ ቃል ዘመለኮት፡ እንዘ ይብል፡ "ሞአ አንበሳ፡ ዘእምነገደ ይሁዳ!"፥ ወበቃለ ትንቢት፡ ዘተነግረ፡ በእንተ ድንግል ማርያም፡ እንዘ ይብል፡ "ኢትዮጵያ፡ ታበጽሕ፡ እደዊሃ፡ ኀበ እግዚአብሔር!"።

ነአምን፡ ከመ ንሕነ፡ ወራስያነ መንግሥቱ፥ ወካህናቲሁ ለእግዚአብሔር፡ በእንተ ወልድናነ፡ በዘውእቱ ዘተከለልነ፡ በክብረ ልደት እምእግዚአብሔር፡ በመንፈስ፡ እንበይነ ጸጋሁ፡ ዘኪዳኑ ቅዱስ።

ነአምን፡ ከመ ብነ ይደልወነ፡ ንሄሉ በንስሓ፡ እንበለ ፅርዓት፡ ለሥርየተ ኃጢአት፥ ወበተመጥዎተ ሥጋሁ፥ ወደሙ፡ ለኢየሱስ ክርስቶስ፡ ለአጽንዖተ ዝንቱ ወልድናነ፥ ወለትውክልተ ውርስናነ ዘመንግሥቱ፥ ወለዝልፈተ ተልእኮትነ ንጹሕ።

"ነአምን፡ ከመ ውእቱ ሃይማኖትነ ዘኢትዮጵያውና፡ ገሃደ ይወጽእ፥ ወቅድስናሁ፡ ይትአወቅ፡ በምግባሪነ ዘኢትዮጵያውና፡ ዘንፈጽም፡ በተዋሕዶተ ፍቅርነ፡ ለኢየሱስ ክርስቶስ፥ ወለድንግል ማርያም።

ነአምን፡ ከመ እግዚአብሔር ውእቱ፡ ዘጸሓፈ ኢትዮጵያውናነ ዘኪዳን ቅዱስ፡ በልቦናነ፥ ወመሀረነ፥ ወረሰየነ፡ ንዕቀቦ በህልዎትነ፡ በእንተ ቃለ ኪዳኑ። ለዓለመ ዓለም፤ አሜን።

ማለትም፡

እግዚአብሔር፡ ለሰው ልጆች፡ የሰጣቸውን ቃል ኪዳናት፡ ጠብቆ በኖረው፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታችን እናምናለን።

አምላካችን፡ ይህን ኢትዮጵያዊ ሰውነት፡ በመጀመሪያው የፍጥረት ዘመን፡ በአዳምና ሔዋን ሥርዓተ ጋብቻ፡ በኪዳነ ልቦና መሠረተው፤ ከዚያም፡ በኖኅ ቀስተ ደመና፥ በመልከ ጼዴቅ ቍርባንና በአብርሃም ግርዛት፡ ገንብቶ አሳደገው፤ በመካከለኛውም የሕግ ዘመን፡ በሙሴ ጽላትና በዳዊት ዙፋን አዋቅሮ፣ የኢትዮጵያዊቷን ንግሥት፡ የማክዳንና የእስራኤላዊዉን ንጉሥ፡ የሰሎሞንን የዘር ሓረጎች በማዋሓድ፡ በኪዳነ ኦሪት አከናወነው፤ በመጨረሻውም የሕይወት ዘመን፡ ከዚህ ምሉእ ትውልድ ከተገኘችው፡ ከድንግል ማርያም በተወለደው ልጁ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም አጽንቶና ዘለዓለማዊዉን ዘውድ አቀዳጅቶ፡ በኪዳነ መንፈስ ቅዱስ ፈጸመው።

ኢትዮጵያ፡ እንዲህ በቀጠለው፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊው ሰውነት፡ ቤተ ሕዝቧን፥ ቤተ ክህነቷና ቤተ ምልክናዋን፡ አንድ አድርጋ የኖረች፡ የእግዚአብሔር መንግሥት እንደኾነች እናምናለን።

እርሱ፡ "ክርስቶስ" ተብሎ፡ እኛን፡ "ክርስቲያን" ያሰኘን፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በቀደመው ዘመን፡ ምሳሌው ኾኖ በተገለጠው፡ በመልከ ጼዴቅ ኢትዮጵያዊነትና ሹመት፡ ከሴም፥ ከካምና ከያፌት ዘሮች ተወልዶ፡ የዘለዓለም ካህናችንና ንጉሣችን እንደኾነ እናምናለን።

እርሷ፡ "ኢትዮጵያ" ተብላ፡ እኛን፡ "ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት" ያሰኘችን፡ ድንግል ማርያም፡ አምላክን በመውለዷ፡ አማናዊቷ የሕይወት ዛፍ፥ የሕያዋን እናትና ዘለዓለማዊቷ ታቦተ ጽዮን፥ የሰማይና የምድር ንግሥትም እንደኾነች እናምናለን።

አረንጓዴ፥ ብጫ፥ ቀይ የኾነው፡ የቀስተ ደመና ምልክት፡ በኖኅ አማካይነት፡ ከእግዚአብሔር የተቀበልነው፡ የዘለዓለም ሰንደቅ ዓላማችን እንደኾነ እናምናለን።

የቅዱሱ ኪዳን ፍጻሜ ለኾነው፡ ለኢየሱስ ክርስቶስ የተነገረው፡ "ከይሁዳ ነገድ የኾነው አንበሳ፡ ድል ነሣ!" የሚለው፡ መለኮታዊ ቃልና ለድንግል ማርያም የተነገረው፡ "ኢትዮጵያ፡ እጆቿን፡ ወደእግዚአብሔር ትዘረጋለች!" የሚለው ትንቢታዊ ቃል፡ ከአምላካችን ያገኘነው፡ የዘለዓለም ማኅተማችን እንደኾነ እናምናለን።

"በቅዱሱ ኪዳን ጸጋ፡ ከእግዚአብሔር፡ በመንፈስ የመወለድን ክብር ስላገኘን፡ በዚህ ልጅነታችን፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ወራሾችና አገልጋዮች እንደኾንን እናምናለን።

"ይህን ልጅነታችንን፡ አጽንተን ለመጠበቅ፥ የመንግሥቱ ወራሽነታችንን ለማረጋገጥና ንጹሕ አገልግሎታችንን ለመቀጠል፡ ኃጢኣታችንን፡ ዘወትር፡ በንስሓ እያጠራንና የክርስቶስን ሥጋና ደም እየተቀበልን መኖር እንዳለብን እናምናለን።

የኢትዮጵያዊነት ሃይማኖታችን፡ በይፋ የሚገለጠውና ተለይቶ የሚታወቀው፡ በኢየሱስ ክርስቶስና በድንግል ማርያም ፍቅር ኾነን በምንፈጽመው፡ የኢትዮጵያዊነት ምግባራችን እንደኾነ እናምናለን።

የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነታችንን፡ በየልቦናችን ጽፎ ያስተማረን፥ ጠብቀነው እንድንኖር ያደረገም፡ እንደቃል ኪዳኑ፡ እግዚአብሔር እንደኾነ እናምናለን።ለዘለዓለሙ፤ አሜን።

፫ኛ፡ አ አቡነ እግዚአብሔር! ነአኵተከ እግዚኦ! ወንሴብሐከ፤ ንባርከከ እግዚኦ! ወንትአምነከ፤ ንገኒ ለከ እግዚኦ! ወንትቀነይ ለስምከ ቅዱስ፤ ንሰግድ ለከ፤ አ ዘለከ፡ ይሰግድ ኵሉ ብርክ፤ ወለከ ይትቀነይ ኵሉ ልሳን። አንተ ውእቱ፡ አምላከ አማልክት፤ ወእግዚአ አጋእዝት፤ ወንጉሠ ነገሥት፤ አምላክ አንተ፡ ለኵሉ ዘሥጋ፤ ወለኵላ ዘነፍስ። ወንጼውዐከ፡ በእንተ ዘተወከፍከ፡ ዝንቱ ጸሎትነ፡ በቤዝዎቱ ለወልድከ፡ ዘመሀረነ ለሊሁ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ እንዘ ይብል፡ 'አንትሙሰ፡ ሶበ ትጼልዩ፡ ከመዝ በሉ፡-

‹አቡነ ዘበሰማያት! ይትቀደስ ስምከ፤ ትምጻእ መንግሥትከ፤ ወይኩን ፈቃድከ፡ በከመ በሰማይ፣ ከማሁ በምድር፤ ሲሳየነ፡ ዘለለዕለትነ፡ ሀበነ ዮም፤ ኅድግ ለነ፡ አበሳነ፥ ወጌጋየነ፡ ከመ ንሕነኒ ንኅድግ፡ ለዘአበሰ ለነ፤ ኢታብአነ እግዚኦ! ውስተ መንሱት፤ አላ አድኅነነ፥ ወባልሃነ፡ እምኵሉ እኩይ፤ እስመ ዚአከ፡ ይእቲ መንግሥት፣ ኃይል፥ ወስብሓት፤ ለዓለመ ዓለም!› ወበእንተ ዘአብዛኅከ ለነ፡ ኂሩትከ፣ ወዘገበርከ ለነ፡ ምሕረትከ፣ ወዘፈጸምከ ለነ፡ ፍቅርከ፣ ወዘወሀብከነ ጸጋከ፡ ለከዊነ ነፍስነ ወሥጋነ።

ወረደ ለነ፡ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ፡ ውስተ ኵሉ ዓለም፣ በምክንያተ ቤዛ ወልድከ መድኅን፡ ዘተወልደ እምቅድስት ድንግል ማርያም። በእንተዝ፡ ኮነ ይእዜ፡ ዘትሄሉ አንተ፡ በምድር፣ ወአኮ በሰማይ ባሕቲቱ። ወዓዲ ተቀደሰ ስምከ፡ በምድር። ወመጽአት መንግሥትከ። ፈቃድከ፡ ዘኮነ በሰማይ፥ ከማሁ፡ ኮነ በምድርኒ።

አስተዳለውከ በሥነ ፍጥረት፡ ምግበ ሥጋነ፡ ዘይበቍዕ፡ ለመፍቅደ ኵሉ ህልዎትነ፣ ወአኮ ሲሳይ ዘለለዕለትነ ባሕቲቱ። ወመጦከነ በኵሉ ጊዜ፡ ሥጋ ወልድከ ቅዱሰ፥ ወደሞ ክቡረ፡ ዘኮነ ለነ፡ ምግበ ነፍስ፥ ወመድኃኒት፡ ዘይረስየነ ሕያዋነ ዘለዓለም፤ ወበውእቱሰ፡ ደምሰስከ፥ ወኃደግከ ለነ፡ ኵሎ ኃጢአተነ፥ ወአበሳነ ግሙራ፣ ወዘኢ.ማእዜ፤ ወከማሁ አባሕከነ፡ ከመ ንሕነኒ ንኅድግ ኵሎ፡ ለዘአበሰ ለነ።

ወአልዓልከነ፡ በልደተ መንፈስ ቅዱስ ዘጥምቀት፡ በዘውእቱ በጻሕነ፡ ከመ ንኩን ውሉድከ፥ ወአዋልድከ፤ ወበጸጋከ ዘንስሓ።

ወአውጻእከነ እመንሱት ዘዘዚአሁ፤ ወአድኃንከነ እምኵሉ እኩይ፤ ወሞእክዎ ለዲያብሎስ፤ ወአሰሰልከ ለሞት፤ ወበእንተ ዝንቱ፡ አሠለጥከነ ንሄሉ፡ በሕይወተ ትንሣኤከ።

አ እግዚኦ! ንሴብሓከ ወትረ፡ በእንተ ኂሩትከ፣ ወምሕረትከ፣ ወፍቅርከ፣ ወጸጋከ፡ ዘአፈወይከነ፡ በዘኢይትከሃል፡ ይትነገር መጠኖሙ፤ ወዓዲ፡ በእንተ ዘትሁበነ፡ ኵሎ ዘንፈቅድ፡ እንዘ አኮ ዘሰአለከ።

ንጸንሕ፡ በከመ አሰፈውከነ፡ ለምጽአተ ዛቲ መዋዕል፡ እንተ ባቲ ትኄንን መንግሥትከ አማናዊት፡ ዘንጉሥነ ኢየሱስ ክርስቶስ፥ ዘተብህለ፡ 'ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ!' ወንሄሉ ንሕነ፡ ይእዜ፡ በውስቴታ፡ ከመ ትትረአይ፥ ወትሰፍን በገሃድ፡ በዝንቱ ዓለም፡ እምድኅረ ትሜርዎሙ ለእከይ፥ ወለኃጢኣት፥ ወለሞት። እስመ ለከ፡ ኃይል፥ ወስብሓት፥ ወመንግሥት፤ ይእዜኒ፥ ወዘልፈኒ፥ ወለዓለመ ዓለም፤ አሜን።

ማለትም፡

አባታችን እግዚአብሔር ሆይ! እናመሰግንሃለን፤ አቤቱ! እናወድስሃለን፤ እንቀድስሃለን፤ አቤቱ! እንታመንብሃለን፤ እናገንሃለንም፤ ጕልበት ኹሉ፡ ለአንተ ይሰግዳል፤ አንደበትም ኹሉ፡ ወደአንተ ይጮሃል። አንተ፡ የአማልክት አምላክ ነህ፤ የገዢዎች ገዢ ነህ፤ የንጉሦችም ንጉሥ ነህ። አንተ፡ የሥጋዊው ኹሉ፥ የነፍሳዊዉም ወገን ኹሉ፡ ፈጣሪ ነህ።

"እናንተ ስትጸልዩ፡ ‹የሰማዩ አባታችን ሆይ! ስምህ ይቀደስ!መንግሥትህ ትምጣ! ፈቃድህ፡ በሰማይ እንደኾነች፡ እንዲሁ፡ በምድር ትኹን! የየዕለቱን ምግባችንን፡ ስጠን ለዛሬ! ኃጢኣታችንንና በደላችንን፡ ይቅር በለን! እኛም የበደሉንን፡ ይቅር እንደምንል! አቤቱ፡ ወደፈተና አታግባን! ከክፉው ኹሉ፡ አድነን እንጂ! ይህች መንግሥት፡ የአንተ ናትና፤ ኃይልና ምስጋናም፤ ለዘለዓለሙ።› በሉ" ብሎ፡ ልጅህ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ያስተማረንን ጸሎታችንን፡ በእርሱው ቤዛነት ተቀብለህ፡ ለነፍሳችንና ለሥጋችን፡ ቸርነትህን አበረከትህልን፤ ምሕረትህን አደረግህልን፤ ፍቅርህን ፈጸምህልን፤ ጸጋህንም ሰጠኸን። ስለዚህ፡ እኛም፡ አኹን፡ እንደዚሁ፡ ስምህን እየጠራን፡ ይኸው እናመሰግንሃለን።

ከቅድስት ድንግል ማርያም፡ በተወለደው ልጅህ መድኃኒትነት፡ የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ፡ በዓለሙ ኹሉ ወረደልን። ስለዚህ፡ በሰማይ ብቻ ሳይኾን፡ ዛሬ፡ በምድርም፡ የምትኖር ኾንህ። ስምህ፡ በምድርም ተቀደሰ። መንግሥትህም፡ መጣችልን። በሰማይ የኾነው ፈቃድህ፡ በምድርም፡ እንዲሁ ኾነ።

የዕለት እንጀራችንን ብቻ ሳይኾን፡ በዕድሜአችን ኹሉ የሚያስፈልገንን፡ ምግበ ሥጋ፡ በሥነ ፍጥረት አዘጋጀህልን። ለዘለዓለም፡ ሕያዋን የሚያደርገንን፥ መድኃኒትና ምግበ ነፍስ የኾነንንም፡ የልጅህን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም፡ ለዘወትር ሰጠኸን። በእርሱም፡ ኃጢአታችንንና በደላችንን ኹሉ፡ ለመቼውም ጊዜ፡ ደምስሰህ፡ ፈጽመህ ይቅር አልኸን። እኛም፡ የበደሉንን ኹሉ፡ ይቅር እንድንል አስቻልኸን።

የአንተ ልጆች ለመኾን የበቃንበትን፡ የጥምቀትን ልደትና የንስሓን ጸጋ አደልኸን።

ከማናቸውም ፈተና አውጥተኸንና ከክፉው ኹሉ አድነኸን፣ ዲያብሎስንና ሞትንም ድል አድርገህ፡ በትንሣኤህ ሕይወት ለመኖር አበቃኸን።

ጌታ ሆይ! ሊነገር ስለማይቻል ቸርነትህና ምሕረትህ፥ ፍቅርህና ጸጋህ፥ እንዲሁም፡ የሚያስፈልገንን ኹሉ፡ ሳንለምንህ ስለምትሰጠን፡ ዘወትር እናመሰግንሃለን።

"ከይሁዳ ነገድ የኾነው አንበሳ፡ ድል ነሣ!" በተባለው፡ በንጉሣችን፡ በኢየሱስ ክርስቶስ፡ ዛሬ የምንኖርባት፡ የእውነት መንግሥትህ፡ ክፋትን፥ ኃጢአትንና ሞትን፡ ፈጽማ አጥፍታ፡ ለግዙፉ ዓለም፡ በገሃድ የምትገለጥበትንና በይፋ የምትሰፍንበትን ጊዜ፡ እንደተሰፋ ቃልህ እንጠብቃለን። ኃይልና ምስጋና፥ መንግሥትም፡ የአንተ ናቸው፤ ዛሬም፥ ዘወትርም፥ ለዘለዓለሙ፤ አሜን።

፩ኛ. ኦ ማርያም እምነ! ንብለኪ፡ "ሰላም ለኪ!" በሰላመ ቅዱስ ገብርኤል መልአክ። ድንግል፡ በኅሊናኪ፤ ወድንግል፡ በሥጋኪ። ይደልወኪ፡ ዝ ሱላሜ፣ እስመ ኮንኪ አንቲ፡ እሙ ለእግዚአብሔር ጸባዖት፡ በእንተ ዛቲ ንጽሓ ባሕርይኪ።

አንቲ ይእቲ፡ ሔዋን ቅድስት፥ ወቡርክት፡ እምኵሎን አንስት፡ በእንተ ዘአሥረፀ ማሕፀንኪ፡ ፍሬሁ ዘዕፀ ሕይወት፡ በዘውእቱ ኮነ፡ አዳምሁ ቅዱስ።

ተፈሥሒ! ኦ ንግሥትነ፡ በሰማይ ወበምድር! እስመ ዘተወደስኪ ጥንት፡ በአፈ ነቢያት፣ እንዘ ይብሉኪ፡ "ኢትዮጵያ፡ ታበጽሕ እደዊሃ፡ ኀበ እግዚአብሔር!" ወንሕነኒ፡ በዘሀልዎትነ፡ እንዘ ንብለኪ፡ "እምነ ጽዮን!"

ንዌድሰኪ ወትረ፡ እንዘ ንብል፡ "ብፅዕት አንቲ፡ ኦ ምልዕተ ጸጋ!" እስመ ዐተበ እግዚአብሔር፡ ኪዳኖ ዘምሕረት፡ ለዓለመ ዓለም፡ በዘአጥረየኪ አንቲ፡ ለምክንያተ ድኅነትነ።

ነአምን፡ ከመ ኢተግሕሠ ክመ እምኔነ፡ ማሕፀንተኪ፡ በአምጣነ እንተ ኢተግሕሠ፡ እምፍቁር ወልድኪ፤ እስመ አንቲ ይእቲ፡ እምነ ዘምሕፅና፣ ወንሕነ፡ ውሉድኪ፥ ወአዋልድኪ፡ ዘምሕፅና፡ በቃለ አማሕፅኖ ዘወልድኪ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ አምላክነ፥ ወመድኃኒነ።

ነአኵቶ ለእግዚአብሔር ልዑል፡ አቡነ ኄር፡ በእንተ ዛቲ ኂሩቱ፡ ዘተገብረት ለነ። ለዓለመ ዓለም።

ማለትም፡

እናታችን ማርያም ሆይ! በመልአኩ፡ በቅዱስ ገብርኤል ሰላምታ፡ "ሰላም!" እንልሻለን። በአሳብሽ፡ ድንግል ነሽ፤ በሥጋሽም፡ ድንግል ነሽ። በዚህ፡ የንጽሕና ባሕርይሽ፡ የአሸናፊው፡ የእግዚአብሔር እናት ኾነሻልና፡ ሰላምታ፡ ለአንቺ ይገባል።

ማሕፀንሽ፡ የሕይወት ዛፍ ፍሬ የኾነውን፡ ቅዱሱን አዳም ስላስገኘ፡ አንቺ፡ ከሴቶች ኹሉ ተለይተሽ፡ የተባረክሽ፡ ቅድስቲቱ ሔዋን ነሽ።

ቀድሞ፡ በነቢያት፡ 'ኢትዮጵያ፡ እጆቿን፡ ወደእግዚአብሔር ትዘረጋለች!' የተባልሽ፥ እኛም፡ 'እናታችን ጽዮን!' ስንልሽ የኖርን፡ በሰማይና በምድር፡ ንግሥታችን ሆይ! ደስ ይበልሽ!"

እግዚአብሔር፡ አንቺን፡ የድኅነታችን ምክንያት አድርጎ፡ ኪዳነ ምሕረቱን፡ ለዘለዓለም ፈጽሟልና፡ 'ጸጋን የተመላሽ፡ ብፅዕት ነሽ!' እያልን፡ ዘወትር እናወድስሻለን።

በአምላካችንና በመድኃኒታችን፡ በኢየሱስ ክርስቶስ፡ አንቺ፡ ለእኛ፡ 'የአደራ እናታችን!'፥ እኛም፡ ለአንቺ፡ 'የአደራ ልጆችሽ!' ነንና፡ ከተወደደው ልጅሽ ያልተለየው እናትነትሽ፡ ከእኛም፡ ምንጊዜም፡ እንደማይለየን እናምናለን።

ይህን ያደረገ፡ ቸሩ አባታችንን፡ ልዑል እግዚአብሔርን፡ እናመሰግነዋለን። ለዘለዓለሙ፤ አሜን።

\+ + +

ይህን የአዋጅ ቃል፥ ለመስማትም ኾነ ለማንበብ፥ በውስጣችሁ፥ የእግዚአብሔር ሃይማኖት ኖሯችሁ፥ ያ ጸጋ ላቀረበላችሁ፥ ለዚህ ዕድል፥ እየራሳችሁን፥ በፈቃዳችሁ ላበቃችሁ፥ በዓለም ላላችሁ፥ የሰው ወገኖች ኹሉ!

እግዚአብሔር ወልድ [መሢሕ] ኢየሱስ ክርስቶስ፥ በቀኙ ባለው ዙፋኗ ላይ ከተቀመጠችው፥ ቅድስት እናቱ ድንግል ማርያም ጋር ኾኖ፥ በቅዱስ መንፈሱ፥ ለእያንዳንዳችሁ፥ በግል፥ እንዲህ ይላችኋል፥-

"ከመጀመሪያዎቹና ከመጨረሻዎቹ አዳም እና ሔዋን ልጆቼ፥ ላገኙኋችሁ፥ ለእናንተ፥ ለምወድዳችሁ፥ ወንዶችና ሴቶች፥ የልጅ ልጆቼ!

ስሜ ስለተጠራባት፥ ስለእናቴ: ስለኢትዮጵያ፤ ስለእውነቴና ስለመንግሥቴም፥ የፍርድ ጵዋዬ ሞልቶ፥ ዳኝነቴን፥ ለዓለሙ ኹሉ፥ ዳግመኛ ላሳውቅ፥ <u>የወሰንሁበት ቀን እነሆ</u>። ካለማመናችሁ የተነሣ፥ ተሠውራባችሁ የቆየችውን፥ እርሷንና ልጆቿን፤ እውነቴንና መንግሥቴንም፥ በእሱ፥ እንደገና፥ ገሃድ አደረግሁ።

የኖኅን ጊዜ ለሚመስለው፥ ለዚህ ዘመናችሁ፥ የእናቴና የእኔ ባለአደራ በኾነው አገልጋያችን እጅ የላክሁት፥ የአዋጅ ቃሌ ይኸውላችሁ!

\+ \+ \+

የምታውቋቸውን እውነታዎች፡ ላስታውሳችሁ፡-

ከኹሉ አስቀድሜ፡ ይህን ፍጥረተ-ዓለም አሳምሬ ሠርቼና አዘጋጅቼ ካጠናቀቅሁ በኋላ፡ የእኔን የመልኬን ዘውድ፡ በፍቅር በማቀዳጀት፥ የእኔን ልብሰ መንግሥት፡ በክብር በማጐናጸፍ፥ ደግሞም፡ የእኔን በትረ ሥልጣን፡ በሙሉነት በማስጨበጥ፥ በእኔ ዘለዓለማዊ ዙፋንም ላይ፡ በአዋጅ በማስቀመጥ፡ የእኔ፡ የሦስቱ አካሎቼና ባሕርዮቼ ክፋይ በኾኑት፡ በሥጋ፥ በነፍስና በመንፈስ፡ የተዋሐዶ ምሥጢር፡ አንድ አድርጌ ፈጥሬ፡ ወደዚች ምድረ ገነት አመጣኋችሁ።

ከዚያ ቀጥዬ፡ ከእኔ ከፈጣሪያችሁና ከአባታችሁ፡ ከተሰጣችሁ፡ የተፈጥሮ ባሕርያችሁ የተነሣ፡ እኔን መስላችሁ፥ እኔንም አኽላችሁ እንድትገኙ በበቃችሁበት፡ በዚያ፡ በደገኛው እውቀትና ሥርዓት፥ በመልካሙም ሕይወት ለመኖር እንድትችሉ አደረግኋችሁ።

እናንተ ግን፡ ገና፡ ከመጀመሪያዎቹ ወላጆቻችሁ፡ ከአዳምና ሔዋን አንሥታችሁ፡ በዚያ እውቀትና ሥርዓት በመኖር ፋንታ፡ ያን ትታችሁ፡ ከዚያ፡ ከመለኮታዊው ደግነት ይልቅ፡ ወደሰይጣናዊው ክፋት አዘነበላችሁ፤ የእየራሳችሁንም የፍልስፍና አሠራር እየተካችሁ፡ ያንንም እየተከተላችሁ፡ ይኸው ትኖራላችሁ። በዚያ የስሕተት ጐዳና ላይ የተጓዙት የቀደሙት ምዝላቶቻችሁ፡ እንደተጎዱና እንደጠፉ ሰማችሁ፤ ዛሬም፡ ያ ጽዋ እየደረሰባቸው ያለፉትን፥ እናንተም፡ የዚያ ዕድል ተካፋዮች ኾናችሁ፡ የኹሉንም ውጤትና ዋጋ፡ በገዛ ዓይኖቻችሁ እያያችሁ ትገኛላችሁ።

ያ ኹሉ የደረሰውና እየደረሰ ያለው ጠንቀኛ ኹኔታ፡ መቀጣጫ ሳይኾናችሁ ቀርቶ፡ ይኸው፡ አኹንም፡ እናንተ፡ እየራሳችሁን፡ "አረማዊ፥ አሕዛብ፥ ሃይማኖተ አልባ፥ አስማተኛ፥ ጣዖታዊ፥ ጃኢን፥ ዞሮአስትሪያን፥ ድሩኢድ፥ ባሓኢ፥ ኮንፉሺያን፥ ሲክ፥ ታኦ፥ ዊካ፥ ሒንዱ፥ ቡዲስት፥ ሺንቶ፥ እስላም፥ ይሁዲና ክርስቲያን" እያላችሁ በመጥራት፡ በጾታና በዘር፥ በቀለምና በመልክ፥ በእምነትና በባህል፥ በእውቀትና በሙያ፥ በሀብትና በኃይል፥ በስያሜና በዜግነት፡ እየራሳችሁን ከፋፍላችሁ፡ እርስ በእርሳችሁ፡ በጥላቻና በጠብ ተለያይታችሁ፡ በመተናነቅና በመዋጋት፥ በመጋደልና በመጨራረስ ላይ ትኖራላችሁ።

በመደምደሚያ ቃሌም፡ የምላችሁ ይህ ነው፡- በመጀመሪያ፡ እናንተን መፍጠሬ ብቻ ሳይኾን፡ ከተፀነሳችሁበት ማሕፀን ጀምሮ ሳልለያችሁ፡ በተፈጥሮ ባሕርያታችሁ ውስጥ ተገኝቼ፡ እነሆ፡ እስካኹን፡ ኹሉን እየገለጽሁላችሁ፡ ዐብሬአችሁ አለሁ።

ኹለተኛ፡ በጥሩው ሥርዓትና በፍጹሙ ጸጥታ በሚካኼደው፡ የሥነ ፍጥረት ሥራዬና በወላጆቻችሁ አማካይነት፥ ያም፡ የማይበቃ በመኾኑ፡ ነቢያቶቼን በመላክ፡ ስለደግነትና ስለክፋት፥ ስለእውነትና ስለሐሰት፥ ስለልማትና ስለጥፋት፥ በመጨረሻም፡ ስለሕይወትና ስለሞት፡ ያለማቋረጥ፡ በየአፍታው፡ በአባትነት ፍቅሬ፡ ስነግራችሁና ሳሳውቃችሁ፥ ሳስተምራችሁና ስመክራችሁ፥ ስገሥጻችሁና ሳስጠነቅቃችሁ፥ እምቢ ስትሉኝም፡ ይኸው ግብራችሁ፡ ያስከተለባችሁን ቅጣት እያየሁና በምሕረቴ እየመለስሁላችሁ ቆየሁ።

እናንተ ግን፡ ይህን ኹሉ አድርጌላችሁ፡ ቃሌን ተቀብላችሁና መልእክቴን ሰምታችሁ፡ ከክፉው ወደደጉ፡ እየተጸጸታችሁ፡ በንስሓ በመመለስ፥ እውነቴንና መንግሥቴንም በመሻት፡ እኔን ወደመምሰሉ በመጓዝ ፋንታ፡ በክፋታችሁና በሓሰታችሁ፥ በጥፋታችሁና በሞት አካኼዳችሁ ቀጥላችሁ፡ እየራሳችሁንና ህልውናችሁን፡ ወደመጨረሻው ድምሳሴ ሊጥል ወደተቃረበው የገደል አፋፍ ደርሳችሁባት የነበረችውን ቀውጢ ሰዓት አየሁ። የተስፋ ቃሌንም አስታወስሁ።

በመጨረሻ፡ የሰብአዊው ፍጡር ህልውና፡ በኖኅ ዘመን በኾነው ዓይነት ሊያበቃ፡ ጊዜው ያለቀበት፡ የፍርድ ሚዛኔ፡ በድፋት ሊያጋድል በተቈረጠባት፡ በዚያች ወሳኝ ሰዓት፡ በፍጡራን ዘንድ፡ "ይኾናል!" ተብሎ ያልታሰበ፥ እኔ ግን፡ እጠብቀው የነበረ፡ አንድ፡ ዕፁብ ድንቅ ነገር ኾነ! እርሱም፡ ከእናንተ፥ በተለይ፡ ከሴቶቹ፡ ጠብቄው በነበረው፥ ዳሩ ግን፡ ላየው ባልቻልሁት፥ በአስተሳሰብና በእውቀት፥ በእምነትና በምግባር ፍላጎቷና ምርጫዋ ረገድ፡ እኔን ከሚያስመስለውና ከሚያሳክለው የተፈጥሮ ማዕርግ፡ ራሷን ያበቃች፥ ወደጥፋቱ ፍጻሜ ሊዳረግ፡ አልቆለት ለነበረውም ፍጥረተ-ዓለም መድኃኒት የኾነች፡ አንዷት ድንግልን፡ ከመካከላችሁ ማግኘቴ ነው።

እርሷን በማግኘቴ፡ እናንተን፡ ከዚያ የመጨረሻ የጥፋት ድምሳሴ ለማዳን ስል፡ እነሆ፡ በእርሷ አማካይነት፡ እንደእናንተ ሰው ኾኜ፡ ራሴ፡ ወደእናንተ መጣሁ፤ መጥቼም፡ አኹን ደግሞ፡ በአካለ ሥጋ ተገልጬ፡ ማንነቴን ያረጋገጠላችሁን፡ የቸርነትና የማዳን ሥራዬን እየፈጸምሁላችሁ፡ በተፈጥሮ ስለሰጠኋችሁ፡ ስለመልካሙ እውቀቴና ሥርዓቴ፡ እንደቀድሞው፡ መላልሼ ነገርኋችሁ፤ አሳወቅኋችሁ፤ አስተማርኋችሁ፤ መከርኋችሁ፤ ገሠፅኋችሁ፤ አስጠነቀቅኋችሁ፤ እምቢ ስትሉኝም፡ እናንተንና ሥራችሁን ሳይኾን፡ ከአጠገቤ፡ ምንጊዜም ያልተለየችኝን እናቴን፡ በቤዛነት በመመልከት፡ እየታገሥኋችሁ፡ በማስተማሬና በምክሬ ቀጠልሁበት።

እናንተ ግን፡ አኹንም፡ ምንም፡ ይህን ኹሉ ባደርግላችሁ፡ ይባስ ብላችሁ፡ አሥራችሁና ገርፋችሁ፡ በእንጨት ላይ ወጥራችሁና ቸንክራችሁ፡ የሾህ አክሊልም አቀዳጅታችሁ፡ ሥጋዬን እየተለተላችሁና ደሜን እያፈሰሳችሁ፡ ዕርቃኔን ሰቀላችሁኝ፤ ገደላችሁኝም። እኔም፡ በዚህ ግፋችሁና ጭካኔያችሁ ሳልቀየም፡ እናንተን አድን ዘንድ፡ በብቅዓቷ፡ እኔን፡ ሰው እንድኾን ያደረገችኝን፥ እናንተንና ፍጥረተ-ዓለሙንም ኹሉ ወክላ፡ እኔን በመውለድ፡ ለመዳናችሁ፡ ምክንያት የኾነቻችሁን እናቴን በማይበት ዓይን አይቻችሁ፡ ይቅር አልኋችሁ።

በፍጻሜውም፡ ከዚህ ኹሉ ሰይጣናዊ ክህደትና ዓመፅ፥ ጥፋትና አመንዝራነት የተነሣ፡ በሰው ዘር ላይ ሠልጥኖ፡ ዓለሙን የገዛውን፡ የክፋትን ጦር፥ የኃጢኣትን ጠንቅና የሞትን ፍዳ፡ በመስቀል መከራዬና በመቊሰል ሥቃዬ፥ በሞት ጽዋዬና በመቃብር ውርደቴ፡ ተቋቁሜላችሁና ተጋድዬላችሁ፡ የዝንተ-ዓለሙ የጦርነት ሰልፍ ማጠናቀቂያ በኾነው፡ በትንሣኤዬ ኃይል፡ እነሆ፡ ኹሉን ዓይነት ባላጋራችሁን አሸነፍሁላችሁ! አስወገድሁላችሁ! ደመሰስሁላችሁም!

እንዲህ፡ ሞትን ድል በማድረግ፡ ከሙታን መካከል፡ ሕያው ኾኜ፡ ከተነሣሁ በኋላ፡ ስለእውነቴና ስለመንግሥቴ፡ ስገልጥላችሁና ስነግራችሁ፥ ሳሳውቃችሁና ሳስተምራችሁ የኖርሁበትን መለኮታዊ መልእክቴን፡ እንደገና፡ ለአርባ ቀናት፡ በማስረዳትና በማብራራት ስሰብክላችሁ ቆይቼ፡ በእግዚአብሔራዊው ክብሬና ገናንነቴ፡ ወደሰማዩ ዙፋኔ፡ እያያችሁኝ ዐረግሁ።

ለአሥር ቀኖች ያህል፡ በአካለ ሥጋ ተለይቻችሁ ቆይቼ፡ የሰጠኋችሁን የተስፋ ቃሌን በመፈጸም፡ ከሙታን ተለይቼ በተነሣሁ፡ በአምሳኛው ቀን፡ በቅዱስ መንፈሴ፡ እንደገና ወደእናንተ ተመልሼ፡ ይኸው፡ ከዚያች ዕለት ጀምሮ፡ ምንጊዜም፥ ዘወትርም፥ ለዘለዓለምም፡ በውስጣችሁና በመካከላችሁ፡ በበለጠ ጥልቀትና ምልዓት፡ ዐብሬአችሁ የምኖር ኾንሁ።

ስለዚች፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ በአደባባይ ወጥቶ የሚመሰክር ሰማዕት፡ እምብዛም ባይገኝ፡ የእውነት ቃሌ፡ በዚህ መልክና ይዘት፡ ቅዱስ መንፈሴ ባደረባቸው፡ በእውነተኞቹና በታማኞቹ ወንዶችና ሴቶች ካህናት ምእመኖቼና ምእመናቶቼ ነቢያትና ሓዋርያት፥ ጻድቃንና ሰማዕታት አማካይነት፡ ያለማቋረጥ፡ ወደእናንተ እንዲደርስ ሳደርግ እንደኖርሁ ታውቃላችሁ።

አኹንም፡ እነሆ ዛሬ፡ "ኢትዮጵያዊ ነኝ!" የሚለው፡ የዚህ፡ የዘመኑ ትውልድ፡ ቤተ ሕዝብ፥ ቤተ ክህነትና ቤተ ምልክና አባል የኾነው፡ ወንዱም፥ ሴቱም፡ ከጥቂቶች በቀር፡ ኹሉም፡ በያለበት፡ የእናቴና የእኔ በኾነው፡ በቅዱሱ ኪዳናችን ላይ፡ በክፋትና በአምልኮ አመንዝራነት ተነሣሥቶ፡ በ፲፱፻፷፮ኛው ዓመተ ምሕረት፥ በ፮ኛው የየካቲት ወር፡ የሓሳዊው መሢሕ፡ መልያ ቍጥር የኾነውን፡ ፮፻፷፮ን አንግቦ፥ በይፋ ሲክደንና ሲያምፅብን፡ መላው ፍጥረተ-ዓለም፡ በግልጽ ተመልክቶታል።

ኢትዮጵያዊው ልጃችንና ካህናችን፡ ኤርምያስ፡ ከሕፃንነቱ ጀምሮ፡ ይህ አዋጅ እስከወጣበት ቀን ድረስ፡ በቅዱሱ ኪዳን፡ "**ኢትዮጵያ**" የተባለችው፡ የእናቴ የድንግል ማርያም እና "**ወልደ እግዚአብሔር**" የተባልሁ፡ የእኔ፡ የኢየሱስ ክርስቶስ **መንግሥት** ዘርፎች በኾኑት፡ በቤተ ሕዝቡ፥ በቤተ ክህነቱና በቤተ ምልክናው ውስጥ፥ ይልቁንም፡ በሢመት በሰጠነውና እኒህን ኹሉ በሚያጠቃልለው፡ የአኵስም ጽዮን ንቡረ እድነቱ ሥልጣን፡ በአኹኑ ጊዜ፡ የዚችው መንግሥታችን፡ ባለአደራዋ ኾኖ፡ ይኸው፡ እያገለገለን ይገኛል።

የዚችው፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥታችን ህልውና፡ በእርሱና እርሱን በመሰሉት፡ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት ሕያው ሰውነት፡ በገሃድ እንዲቀጥል ከማድረጉ ጋር፡ ያን ታላቅ ኃጢአት የፈጸመው፡ ይኸው ትውልድ፡ በንስሓ እንዲመለስ፡ ይኸው አገልጋያችንና ባለአደራችን፡ የፈጸመውን ድካምና ጥረት፡ እናንተና ባዕዱም ኹሉ የተገነዘባችሁት ነው። ዛሬም፡ ይኸው ጽናቱ፡ ይህ የአዋጅ ቃል፡ ለዓለሙ ኹሉ እንዲሰማ አድርጓል።

መንፈስ ቅዱስ የሚያውቀውና የሚቀበለው እውነተኛነት፡ በእርግጥ በናንተ፡ በእያንዳንዳችሁ ዘንድ ካለ፡ እየራሳችሁ፡ በገዛ ፍላጎታችሁና ምርጫችሁ፡ በቅዱሱ ኪዳናችን ላይ ከፈጸማችሁት ግልጽ ክህደታችሁና ዓመፃችሁ፥ ክፋታችሁና የአምልኮ አመንዝርነታችሁ ታላቅ ኃጢአት፡ በፍጹም ንስሓ ለመመለስ፡ የአርባ ዓመት ዕድሜ እንደሚበቃችሁ፡ ኅሊናችሁ እየወቀሰ ከሚነግራችሁ በላይ፡ እንግዴህ ወዲህ፡ ማንም ሊያሳስባችሁ እንደማያስፈልግ፡ እናንተም አትስቱትም።

ስለዚህ፡ ይህ የመሰነባበቻ ቊርጥ ዕድል፡ እነሆ፡ ለኹላችሁም፡ በነፍስ ወከፍ የቀረበላችሁ መኾኑን፡ የምታረጋግጡበትን የመጨረሻ ቃላችንን፡ እናቴም፥ እኔም፡ ልከንላችኋለሁና፡ ለእየራሳችሁ ደኅንነትና በጎነት ስትሉ፡ በዚሁ አገልጋያችንና ባለአደራችን እጅ የቀረበላችሁን መልእክታችንን ተቀበሉት! ስሙት! ለመልካሙ፡ የንስሓ ፍሬም አብቅታችሁ ፈጽሙት!

ይህን በማድረጋችሁ፡ ለዘለዓለማዊው፡ የሥጋና የነፍስ፥ የመንፈስም፡ የግልና የጋራ መልካም ሕይወታችሁ የሚበጃችሁን መንገድ መከተላችሁ ነውና። እንግዴህም፡ ማንም ሊወስድባችሁ፥ ወይም፡ ሊያሳጣችሁ የማይቻለውን፡ የድል አክሊላችሁን ተቀዳጅታችሁ፡ ያለሥጋትና ጭንቀት፥ ያለፍርሃትና ሥቃይ፥ በዘለዓለም ዕረፍትና ሰላም፡ ክብርና ደስታ፥ ኑሯችሁን የምትቀጥሉ ኹኑ!

\+ \+ \+

## "ኢትዮጵያ" ማናት?

በዚህ የአዋጅ ቃል መሠረት፡ መላውን የመናፍስት ወገንና የሰውን ዘር የሚያጠቃልለውን ፍጥረተ-ዓለም በመወከል፡ ቀድሞ፡ በዘመነ ብሉይ ኪዳን፡ "ታበጽሕ እደዊሃ፡ ኀበ እግዚአብሔር!" ደግሞም፡ "ናሁ፡ ድንግል ትፀንስ፤ ወትወልድ ወልደ፤ ወይሰመይ ስሙ፡ አማኑኤል! ዘበትርጓሜሁ፡ 'እግዚአብሔር ምስሌነ'።" ማለትም፡ "እጆቿን፡ ወደእግዚአብሔር ትዘረጋለች!" እንዲሁም፡ "እነሆ፡ ድንግል ትፀንሳለች፤ ወንድ ልጅንም ትወልዳለች፤ ስሙም፡ 'አማኑኤል' ይባላል፤ የዚህም ትርጉም፡ 'እግዚአብሔር፡ ከእኛ ጋር ነው!' የሚል ነው።" ተብሎ፡ ትንቢት የተነገረላት፥

ኋላም፡ በዘመነ ሐዲስ ኪዳን፡ ትንቢቱ ኹሉ ተፈጽሞ፡ "ተፈሥሒ ፍሥሕት! ኦ ምልዕተ ጸጋ! እግዚአብሔር ምስሌኪ፤ ቡርክት አንቲ እምአንስት። ወናሁ ትፀንሲ! ወትወልዲ ወልደ! ወትሰምዪዮ ስሞ፡ 'ኢየሱስ!' ውእቱ ዐቢይ! ወይሰመይ፡ 'ወልደ እግዚአብሔር ልዑል!' ወይሁቦ እግዚአብሔር አምላክ፡ መንበረ ዳዊት አቡሁ፤ ወይነግሥ ለቤተ ያዕቆብ ለዓለም፤ ወአልቦ ማኅለቅት፡ ለመንግሥቱ።" ማለትም፡ "ከሴቶች መካከል፡ የተለየሽ 'ቡርክት' ኾነሽ በመገኘትሽ፡ እግዚአብሔር፡ ከአንቺ ጋር ኾኗልና፥ የደስታ ባለቤትም ኾነሻልና፡ ጸጋን የተመላሽ ሆይ! ደስ ይበልሽ! እነሆ፡ ወንድ ልጅን ፀንሰሽ ትወልጃለሽ! ስሙንም፡ 'ኢየሱስ!' ብለሽ ትሰይሚዋለሽ፤ እርሱ፡ ታላቅ ነው፤ 'የልዑል እግዚአብሔር ልጅ' ተብሎም ይጠራል።

**"እግዚአብሔር አምላክም፡ የአባቱን፡ የዳዊትን ዙፋን ይሰጠዋል፤ በያዕቆብም ወገን ላይ ለዘለዓለም ይነግሣል፤ ለመንግሥቱ፡ ፍጻሜ የለውም።"** ተብሎ በእግዚአብሔር መልአክ፡ በቅዱስ ገብርኤል የተበሠረላት፥

የቅዱሱ ኪዳን ልጆቿም፡ **"መርዓተ አብ፤ ወእመ በግዑ። ብኪ ድኅነ ዓለም፤ ወበወልድኪ፡ ኮነ ሰላም!"** ማለትም፡ **"የእግዚአብሔር አብ ሙሽሪት፤ 'የእግዚአብሔር በግ' የተባለ ልጁም፡ እናት። ዓለሙ ኹሉ በአንቺ ዳነ፤ በልጅሽም፡ ሰላም ኾነ!"** እያሉ የሚዘምሩላት፡ **<u>ድንግል ማርያም ናት።</u>**

"ኢትዮጵያ" የሚለው ስሟ፡ "ኢትዮጲስ" ከተባለው፡ ከመጀመሪያው "መልከ ጼዴቅ" የማንነት ስያሜ የተወረሰ ኾኖ፡ በአኹኑ ጊዜ፡ በተለይ፡ የጣና ሐይቅ ተንጣልሎ የሠፈረበትንና ታላቁ፡ የዓባይ ወንዝ፡ መንጭቶ የሚፈስስበትን፡ የጐጃምን ምድር እየከበበች ላለችው አገር፡ መጠሪያነት የተሰጠው፡ እንዲያው፡ ያለምክንያት አልነበረም፤ እግዚአብሔር፡ አዳምንና ሔዋንን፡ በመልኩ ፈጥሮና ክብሩን አጐናጽፎ፡ መልካሙን ሕይወት እንዲኖሩባት የተከላት፡ "የኤዶም ገነት" የምትገኝባት ክልል በመኾኗ ነው።

ደግሞም፡ ይኸው፡ <u>"ኢትዮጵያ" የሚለው መጠሪያ፡</u> **እግዚአብሔርን የወለደችውን፡ የድንግል ማርያምን ሕያው ሰውነት፥ እንዲሁም፡ አካላዊ የኾነውን ግዙፍ ቦታ፥ ወይም፡ ምድር፥ ወይም አገር የሚያመለክት ብቻ አይደለም፤ ከላይ፡ እንደተገለጠው፡ <u>የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ዐይላና ሰፍና፡ የምታስተዳድርበትን፡ ሰማዩንና ምድሩን የሚያጠቃልለውን፡ መላውን ፍጥረተ-ዓለም ኹሉ እንጂ።</u>**

ከዚህም በላይ፡ "ኢትዮጵያ" የሚለው ቃል፡ ፈጣሪ፡ ለሰብኣዊ ፍጡሩና ለመላው ፍጥረቱ፡ መልካም ህልውና፡ ጥንቱኑ ያሠረፀው መለኮታዊ ፅንሰ አሳብ፥ ያዘጋጀው መለኮታዊ ዕቅዱና የወሰነው መለኮታዊው ግቡ መገለጫ መኾኑ፡ በታየውና በኾነው፥ በተፈጸመውም እውነታ ተረጋግጦ ታውቋል።

ይህ ብቻ አይደለም፤ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ እንደተወሳው፡ እግዚአብሔር፡ "ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት" ከተባሉ፡ ከተለዩ ቤተ ሰቦች ጋር በተካየዳቸው፡ በሰባቱ ቅዱሳት ኪዳናት ላይ ተመሥርቶ የታነጸው፡ የቅዱሱ ኪዳን እምነት፡ ህልውናና እውቅና ያገኘው፡ በዚሁ፡ "ኢትዮጵያ" በሚለው ቃል እንደኾነ፡ አምላካዊው ዜና መዋዕል፡ አበክሮ አስገንዝቧል።

ተደጋግሞ እንደተገለጸው፡ "ኹሉን የፈጠረ፡ አንድ አምላክ አለ!" በሚል እውነት የተከሠተውና የቅዱሱ ኪዳን ፍሬ የኾነው፡ ይህ፡ የኢትዮጵያ ተዋሕዶ እምነት፡ በህልውናው፡ ከክርስትና፥ ይልቁንም፡ አነስተኛ ዕድሜ ካለው፡ ከእስልምና ቀርቶ፡ ቀደም ካሉት፡ ከይሁዲነት፥ ከቡዲዝም፥ ከሒንዱኢዝም፥ ከሺንቶኢዝም እና ከሌሎቹ ጥንታውያን ሃይማኖቶች ይልቅ፡ ወደኋላ፡ አያሌ ሽህ ዓመታትን የሚያስቆጥር የዕድሜ ቅድሚያ እንዳለው፡ በጽሕፈት ምስክርነት ለሚያምነው ዓለም፡ የተቀበላቸውን ቅዱሳት መጻሕፍት፡ በማስረጃነት ማቅረቡ በቂ ይኾናል።

## "እግዚአብሔር" ማነው?

"አብ፥ ወልድ፥ መንፈስ ቅዱስ" ተብሎ፡ በሦስትነት የሚታወቀው እግዚአብሔር፡ ያው፡ አንድ አምላክ የኾነው፡ ፈጣሪ ሲኾን፡ በዚህ የአዋጅ ቃል መሠረት፡ "እግዚአብሔር" የሚለው ቃል የሚያመለክተው፡ መጀመሪያ፡ ከፍጥረት በፊት፡ ከባሕርይ አባቱ፡ ከእግዚአብሔር አብ፡ ያለእናት፡ በመለኮትነት፥ በመጨረሻውም የሕይወት ዘመን፡ ከትስብእት እናቱ፡ ከቅድስት ድንግል ማርያም፡ ያለአባት፡ በሰውነት ተወልዶ፡ የክፋቱና የኃጢአቱ ዋጋ፡ ሞት ኾኖ የማሰነውን (ጠፍቶ የነበረውን) ፍጥረተ ዓለም፡ በቤዛነቱ አድኖና አድሶ፡ ለመልካሙ ሕይወት ካበቃው በኋላ፡ ዛሬ፡ የባሕርይ ሕይወቱ በኾነው፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ተመልሶ፡ ፍጥረተ-ዓለሙን፡ በጸጋው የመላው፡ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።

## "መንግሥት" ምንድን ነው?

በዚህ የአዋጅ ቃል መሠረት፡ "**እስመ ለእግዚአብሔር መንግሥት!**" ማለትም፡ "**መንግሥት፡ የእግዚአብሔር፥ በእግዚአብሔርና ለእግዚአብሔር ናት!**" የሚለውን መለኮታዊ ቃል በመከተል፡ እርሱ፡ ልጁ ኢየሱስ ክርስቶስና እርሷ፡ እናቱ ድንግል ማርያም፡ በሰማያትና በምድር የሚኖረውን፡ ፍጥረታቸውን፡ በአባትነትና በእናትነት፥ በካህንነትና በክህነት፥ በንጉሥነትና በንግሥትነት ለመምራትና ለማስተዳደር፥ ለመንከባከብና ለመለገሥ፥ ለመቈጣጠርና ለመጠበቅ፡ እርሱ፡ ራሱ፡ እግዚአብሔር፡ በመጀመሪያዎቹ አዳምና ሔዋን ሰውነት፡ በግዘፍና በገሃድ የመሠረታትና ያቋቋማት፥ የደመደማትና ያከናወናት፡ ሕያውትና ዘለዓለማዊት የሥርዓቱ አቋም ናት።

እንግዴህ፡ ዓለም ሳይፈጠር የነበረችው፥ ዓለም ከተፈጠረ በኋላም፡ በህልውናዋ የቀጠለችው፥ ዛሬም ያለችው፥ ወደፊትም፡ ለዘለዓለም የምትኖረው፡ ይህች፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡** እነሆ፡ ሰዎች፡ ወስነው በከለሏት አገርና በሰፊው የአህጉራቱ ዓለም ብቻ ሳይኾን፡ በመላው የሰማዩና የምድሩ ፍጥረተ-ዓለም ላይ፡ በይፋ ሰፍና፥ በገሃድም ተገልጣ፡ በሕያውነት የምትገኝ መኾኗን፡ መንፈሳዊውና ሥጋዊው፥ ረቂቁና ግዙፉ ፍጥረት ኹሉ ይወቅ!

## ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ስለመኾኗ።

"**ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ናት!**" ተብሎ ሲነገርና ሲጻፍ፡ ይህን ቃል በሚሰማበትና በሚያነብበት ጊዜ፡ አምኖ ለመቀበል የሚያዳግተውና የሚቃወመው፥ ግር የሚለውና ግራ የሚጋባው፥ እንዲያውም፡ የሚያፌዘውና የሚሣለቀው ሰብአዊው ፍጡር፡ እጅግ ብዙ ሊኾን እንደሚችል ይታወቃል።

እንዲያውም፡ በዚህ ድንግርግር አቋሙ፡ ኹሉም የሰው ዘር እንደተባበረ፡ ይኸው እየታየ ነው። ከዚህም ይባስ፡ ይህን የመሰለውን፡ የተሳሳተ አቋም የተቀበለውና የተከተለው፥ የያዘውና ያጸናው፡ ይኸው ሰብአዊ ትውልድ፡ ራሱን፡ ከእግዚአብሔር በላይ አድርጎ፡ በንቀትና በድፍረት፥ በትምክህትና በዕብሪት፡ "ኢትዮጵያ፡ እኔ ነኝ!። መንግሥቷም፡ እኔ፡ 'መንግሥት' እያልሁ በማቋቋም የማካኺደው አገዛዝ አይደለምን?" እያለ እንደሚደነፋ፡ በምንም መንገድ ማስተባበል፡ ከቶ አይቻልም፤ ይህ ድርጊቱ፡ በተለያየ የርእዮተ-ዓለም ስያሜ፡ በዓለሙ ኹሉ በተንሠራፋት የሰዎች "መንግሥታዊ" የአገዛዝ ስልቶች፡ ይኸው፡ በገሃድና በይፋ ሲፈጸም የሚታይ ነውና።

ይኹን እንጂ፡ "ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት"፡ ይህ፡ ሃይማኖተቢሱ፡ የዘመኑ፡ የዓለሙ ሰብአዊ ትውልድ፡ በየአገሩ ተለያይቶና ተከፋፍሎ፡ በሓሰት ፍልስፍናና በምትሓት የፈጠራት፡ ሰውኛዋ አለመኾኗ፥ በእርግጥም፡ እርሷን፡ በእግዚአብሔር እውነት በማይቀበላትና በሰይጣናዊው ሓሰት በሚቃወማት ትውልድ ዘንድ፡ ልትገኝ ቀርቶ፡ ልትታወቅ እንደማይቻል እሙን (የታመነ) ነው።

አዎን! እርሷ ግን፡ ከላይ እንደተመለከተው፡ በሰማያዊው (በረቂቁ) እና በምድራዊው (በግዙፉ) መላው ፍጥረተ-ዓለም ላይ ሰፍና፥ በእውነተኞቹ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያትም ሕያው ሰውነት ላይ አብርታ፡ እነሆ፡ በህልውናዋ እንደቀጠለች ተገኛለች። ይህ እውነታ፡ በእነዚሁ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት ልጆቿ፡ የክህነት አገልግሎት አማካይነት፡ በተለያዩት የጎዋ ሰሌዳዎቻቸውና መድረኮቻቸው፥ በመጻሕፍታቸውና የሕዝብ መገናኛዎች በኩል በተላለፉትና በተሠራጩት፡ የመንፈስ ቅዱስ መልእክቶቿ፡ ግልጥ ኾኖ እንዲታወቅ ስለተደረገ፣ ይህንም፡ በእግዚአብሔር እውቀት ለመረዳት ለፈለገ ሰብአዊ ፍጡር፡ የእርሷን ምንነትና ማንነት፡ በእግዚአብሔራዊው እውነት ለማረጋገጥ፡ እጅግም አያዳግትም።

ከዚህ የተነሣ፡ "በውኑ፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ናትን?" ለሚለው ጥያቄ፡ "አዎን! ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ናት።" የሚለውን መልስ በመስጠት፡ ይህን፡ የመንፈስ ቅዱስ እውነት፡ ፍጥረተ-ዓለሙ፡ በሃይማኖት ተቀብሎ፡ ሕይወት አድርጎት ይኖረው ዘንድ፡ በዚህ የአዋጅ ቃል፡ መልስ ኾኖ፡ ይኸው፡ ለመጨረሻ ጊዜ እንዲቀርብለት አስፈላጊ ኾኗል።

"ይህ መልስ፡ እንዴት፡ እውነት ሊኾን ቻለ?" ማለትም፡ "ኢትዮጵያ፡ ለዚህ፡ ለእግዚአብሔር መንግሥትነት ታላቅ ጸጋና ክብር፡ የበቃች ኾና ለመገኘት፡ እንደምን ቻለች?" ለሚለው ተከታይ ጥያቄ፡ መልሱ፡ ቀጥተኛና አጭር ነው፤ ይኸውም፡ "የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያና ልጆቿ፡ ኄኖክንና ኖኅን፡ ከነሚስቶቻቸው፥ እነርሱንም እንደመሰሉት፡ እንደቀደሙት ቅዱሳንና ቅዱሳት ወላጆቻቸው ኹሉ፡ "አካኺዳቸውን፡ ከእግዚአብሔር ጋር ስላደረጉ ነው!" የሚል ይኾናል።

ይህም፡ "ለግልና ለቤተሰብ፥ ለጋራና ለኅብረተሰብ ህልውናቸው መሪ አድርገው፡ ሕይወታቸውን የሚኖሩት፡ ከፈጣሪያቸው፡ ከእግዚአብሔር፡ በቅዱሱ ኪዳን ያገኙትንና የተቀበሉትን ቃልና ሥርዓት፡ ያለውልውል በመከተላቸው ብቻ ነው!" ማለት ነው። ከዚያ ውጪና የተለየ የኾነውን፡ ሰውኛውን፥ ወይም፡ ሰይጣናዊዉን አይቀበሉም።

አዎን! የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ ጆሮዎቻቸውን ቀቅረው [በጣም አስጠግተው] የሚያዳምጡት፥ ነፍሳቸውም፡ "እህ!" ብላ፡ በአፍአዊው ሥጋዊ አካሏና በውሳጣዊው መንፈሳዊ ባሕርይዋ የምትሰማው፡ መለኮታዊዉን ድምፅ ብቻ ነው። በእግዚአብሔር መልክ የተፈጠሩበትን ባሕርያቸውን፡ ሳይበርዙና ሳይለውጡ፡ በተፈጥሮ የንጽሕና ጠባዩ ደረጃ፡ ጠብቀውት ስለሚገኙ፡ የእግዚአብሔርን መሪ ድምፅና ቃል ለይተው ለማወቅና ተረድተው ለመቀበል፥ በምግባርም ለመፈጸም፡ ሥጋዊዉም፥ ነፍሳዊዉም፥ መንፈሳዊዉም፡ የተፈጥሮ ኃይሉና ብቅዓቱ አላቸው። እርሱም፡ <u>የእግዚአብሔር እውቀት</u> ነው።

ለዚህ እውነታ፡ ማስተማመኛው፡ መለኮታዊው የሃይማኖትና የምግባር ማስረጃ፡ ይኸው፡ በግልጽ ሲመሰክር ይታያል፤ ይህም ምስክርነት፡ <u>ሌላው፡ በመላው ዓለም የሚኖረው የሰው ዘር፡ በኖኅ ዘመን እንደኾነውና ከዚያም ወዲህ፡ እስካኹን እየኾነ እንደሚታየው፡ የእግዚአብሔርን የቃል ኪዳን እምነትና ምግባር፥ ሥርዓትና አቋም፡ በክፋትና በክህደት፥ በዓመፅና በአምልኮ ምንዝርና፡ ሲተወውና ሲቃወመው፡ እነርሱ፡ ማለትም፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ብቻ፡ ለሰባት ሺህ አምስት መቶ አምስት ዓመታት፡ እስከዛሬ ድረስ፡ ጠብቀውትና አጽንተውት መኖራቸው፤ አኹንም እየኖሩት መገኘታቸውና ወደፊትም፡ በዚሁ ኑሯቸው የሚቀጥሉበት መኾናቸው ነው።</u>

የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ለፍጥረተ-ዓለሙ፡ እንዲህ፡ በገሃድ የተገለጸችባቸውና በሕያውነት ጸንታ፡ በህልውናዋ የቀጠለችባቸው መሠረታውያን ሀብታትና ኃይላት፡ <u>ሰባቱ ቅዱሳት ቃል ኪዳናት</u> ናቸው።

ፈጣሪ፡ ከፍጥረት መጀመሪያ አንሥቶ፡ ከሰብአዊው ፍጡሩ ጋር ያደረጋቸው፡ እነዚህ ቃል ኪዳናት፡ የሰውን ዘር ወክለውና ለደኅንነቱ ምክንያት ኾነው፡ ሊቤዡት፡ ብቅዓት ካገኙ፡ ብርቅ ግለሰቦች ጋራ፡ እግዚአብሔር የተካየደባቸው፡ ሕያዋን ውርሶች ናቸው። ይህ እውነታ፡ ለዝንተ ዓለም ሲወርድ ሲዋረድ በኖረው፡ በኢትዮጵያውያኑና በኢትዮጵያውያቱ ትውፊት ሲነገር የቆየ እንደመኾኑ፡ ዓለም በተቀበላቸው ቅዱሳት መጻሕፍትም ውስጥ ተመዝግቦ ይነበባል።

ቃል ኪዳናቱም፡ የመጀመሪያው፡ በአዳምና ሔዋን ሥርዓተ ጋብቻ፥ ኹለተኛው፡ በኖኅ ቀስተ ደመና፥ ሦስተኛው፡ በመልከ ጼዴቅ የኅብስትና የወይን ቍርባን፥ አራተኛው፡ በአብርሃም ግርዛት፥ አምስተኛው፡ በሙሴ ጽላት፥ ስድስተኛው፡ በዳዊት ዙፋን፥ ሰባተኛውና የመጨረሻው፡ ከድንግል ማርያም በተወለደውና በተሰቀለው፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነትና ማኅተምነት፡ እኒህ፡ የፊተኞቹ ስድስቱ፡ ለዘለዓለማዊነት የበቁበት፡ የመሢሕ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ናቸው።

እዚህ ላይ፡ በተለይ ሊዘከር የሚገባው፡ አንድ ድንቅ ነገር አለ፤ ይኸውም፡ ከመላው የዓለም ሕዝቦች ኹሉ መካከል፡ እንደአንድ የአገር ሕዝብ፡ ለእነዚህ፡ ለሰባቱም አምላካውያት ኪዳኖች፡ በህልውና መኖር፡ ሕያዋን ምስክሮች በመኾን፡ እስከዛሬ ድረስ፡ አጽንተዋቸውና ጠብቀዋቸው ሊቀጥሉ የቻሉ፡ የኢትዮጵያ የቅዱሱ ኪዳን ወንዶችና ሴቶች ልጆች ብቻ መኾናቸው ነው። አረማውያን፥ ወይም፡ አሕዛብ፥ ወይም፡ አይሁድ፥ ወይም ክርስቲያኖች ወይም እስላሞች፥ ወይም ሌሎቹ፡ በዓለሙ ውስጥ ያሉት፡ የተለያዩት ሃይማኖቶች ወገኖች አይደሉም፡ ጠብቀዋቸው የኖሩት።

## ለመኾኑ፡ "የእግዚአብሔር መንግሥት"፡ ምንድን ነው?

የሚታየውን ግዙፍ ሥጋዊ ምድር እና የማይታየውን ረቂቅ መንፈሳዊ ሰማይ ያጠቃለለው፡ መላው ፍጥረተ ዓለም፡ "የእግዚአብሔር መንግሥት" ይባላል። አዎን! የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ይኸው ፍጥረተ ዓለም የሚመራበትና የሚካኼድበት፥ የሚተዳደርበትና የሚጠበቅበት፡ እንከን የሌለው ፍጹሙ፡ የሥነ ፍጥረት ሥርዓት ነው። ሰብአውያን ፍጡሮች፡ ሥጋዊና ምድራዊ፥ ማኅበራዊና የጋራ ህልውናቸውን የሚያራምዱበትንና የሚያከናውኑበትን፡ የአኗኗርና የአገዛዝ ፍልስፍናቸውን ፅንሰ ሓሳብ ያገኙት፡ ከዚሁ፡ የሥነ ፍጥረት፡ አመራርና የእንክብካቤ አያያዝ ከኾነው፡ ከመለኮታዊው ሥርዓትና ዘይቤ መኾኑን ለማወቅ፡ ለማንም የሚሣን አይደለም።

"መንግሥት" የሚለው፡ ነባር ቃል፡ መሠረቱ፡ ግእዝ እንደመኾኑ መጠን፡ ጽንፍ የሌለውንና በምልዓት የሰፈነውን፡ ይህን፡ ዘለዓለማዊ የህልውና ዓለም፡ በሥርዓት ሊመሩና ሊያካኺዱ፡ "ንጉሥ" እና "ንግሥት" ተብለው የሚጠሩ፥ ለፍጥረቱም፡ "አባት" እና "እናት" የኾኑ፡ ባለቤቶችና የበላዮች ያስፈልጉታል። "መንግሥት" ተብሎ፡ "ንጉሥ" እና/ወይም፡ "ንግሥት" የሌሉበት ሥርዓት፡ የለምና። ሊኖርም አይችልምና። እነርሱም፡ ፈጣሪው እግዚአብሔር ኢየሱስ ክርስቶስ እና እርሱን፡ በሰውነት የወለደችው፡ ድንግል ማርያም ናቸው።

በዚህ፡ በግዙፉ፡ ሥጋዊና በማይታየው፡ በረቂቁ፡ ምሥጢራዊና ትንግርታዊ አጠቃላይ ዓለም ላይ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ሰውነት የተገለጠው፡ የፍጥረቱ አስገኚ፥ ባለቤትና መጋቢ እግዚአብሔር፡ ካህኑ ንጉሥ ኾኖ፥ ኢትዮጵያን የኾነችው ቅድስት እናቱ፡ ድንግል ማርያም ደግሞ፡ ካህኒቱ ንግሥት ኾና፡ መላውን ፍጥረታቸውን፡ እስከ ዛሬና ዛሬ፥ ለዘወትርና ለዘለዓለምም፡ በክህነታዊው የምስፍና መሪነታቸው እያስተዳደሩ ይኖራሉ።

ኢየሱስ ክርስቶስ፡ የእግዚአብሔር አንድ አምላክነትና ቅዱስ ሥሉስነት፡ ግዙፍ መገለጫ አካል ሲኾን፥ ድንግል ማርያም ደግሞ፡ እንደመዝሙራዊው ቃል፡ "**እጆቿን፡ ወደእግዚአብሔር ትዘረጋለች!**" የተባለችውና መላውን፡ የሰውን ዘር የወከለችው፡ የኢትዮጵያ ግዙፍ መገለጫ አካል ናት። እንዲህ እንደመኾኗ፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡** ከኀሌ ኵሉ (ኹሉን ማድረግ የምትችል)፥ ምሉዕ በኵለሄ (በኹሉ የመላች) ነች። ስለዚህ፡ በግዙፉ ሥጋዊ ዓለም ኾነ፡ በረቂቁ መንፈሳዊ ዓለም፡ በኹሉም ዘንድ ሠርፃና ሰፍና የምትገኝ ናት።

እንደቅዱሳት መጻሕፍት ቃል፡ እግዚአብሔር አምላክ፡ ግዙፉን ዓለም በፈጠረ ጊዜ፥ አዳምንና ሔዋንንም፡ በአርአያውና በመልኩ በሠራቸው ጊዜ፡ እነሆ፡ በዚያን ጊዜ፡ በእውነት መንፈሳዊት፥ ከሃሌ ኵሉ እና ምሉዕ በኵለሄ የኾነችው፡ የእርሱ መንግሥት ተገለጠች። አዳምና ሔዋንም፡ በመላ ፍጥረተ ዓለሙ ላይ አጼ (ካህኑ ንጉሥ) እና አጼዪት (ካህኒቱ ንግሥት) ኾነው ይሰፍኑ፥ ያስተዳድሩም ዘንድ፡ የመጀመሪያዎቹ እንደራሴዎቹ አድርጎ ቀብቶ አነገሣቸው። (ዘፍጥ. ፩፥ ፳፮-፳፰።)

እነርሱ ግን፡ በተፈጥሮ በተሰጣቸው የፍላጎትና የምርጫ ነጻነታቸው መብት ተጠቅመው፡ ዕድላቸውን በማበላሸት፡ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ፡ የመጨረሻው ሉዓላዊ የኾነውን፡ የማዕርግ ደረጃ፡ በፈቃዳቸው ለቅቀውና ተዋርደው፥ የንጉሥነትና የንግሥትነት መለኮታዊ ክብራቸውንም ተገፍፈው፡ የዲያብሎስ ባሮች፥ ተገዢዎችና አገልጋዮች ኾኑ። "የሰው ልጆች" የሚል ስያሜ የተሰጣቸው ተከታዮቻቸውም፡ በዚሁ፡ የክፋት ዝንባሌያቸውና መንገዳቸው፡ <u>እስከዛሬም</u> ቀጥለውበት፡ የዚያው፡ የክፉው አበጋዝ፡ የአገዛዝ ቀንበር ተሸካሚዎች ኾነው ቀሩ።

በዚህ አንጻር፡ ይህችው የእግዚአብሔር መንግሥት፡ "የእግዚአብሔር ልጆች" በተባሉት፡ ኄኖክንና ሚስቱን፥ ኖኅንና ሓይከልን፥ መልከ ጼዴቅንና ሳሌምን፥ አብርሃምንና ሣራን፥ ሙሴንና ሲጳራን፥ ተነሳሒያኑን ዳዊትንና ቤትሳባን፥ ሰሎሞንንና ማክዳን፣ ኢያቄምንና ሓናን በመሰሉት ታማኞች ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ግለሰቦች ሰውነት፡ ተጠብቃ ቆየች።

እንዲህም የኾነው፡ ለማንኛውም፡ ለተራውም ኾነ ለሌላው፡ ለእያንዳንዱ፡ ለሚፈልጋት ሰብአዊ ፍጡር ኹሉ፡ ይህችው የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ራሷን፡ በቀላሉ ልታስገኝ እንደምትችል አድርጋ በማቅረብ፡ በመጨረሻው የሕይወት ዘመን፡ ከኢትዮጵያዊቷ ቅድስት ድንግል ማርያም በተወለደው፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ቤዛነት፡ በቀደመ ገናንነቷ ተገልጻ፡ በፍጥረተ ዓለሙ ላይ እስክትሰፍን ድረስ ነበር።

## የእግዚአብሔር መንግሥት

## ሥርዓታዊ አቋም (ሕገ መንግሥት) ምንድን ነው?

ቀደም ብሎና ተደጋግሞ እንደተገለጠው፡ "እስመ ለእግዚአብሔር መንግሥት!" ማለትም፡ "መንግሥት፡ የእግዚአብሔር ናት!" የተባለው፡ ያለበቂ ምክንያትና ያለመሠረታዊ መነሻ አይደለም። ፍጥረትን የፈጠረ፡ ማለትም፡ ካለመኖር፡ ወደመኖር ያመጣውና የሚጠብቀው፥ የሚመራውና የሚያስተዳድረው ባለቤቱ፡ እርሱ ብቻ ስለኾነ ነው። ከዚህ የተነሣ፡ ለፍጥረተ ዓለሙ፡ ሌላ መንግሥት ሊኖረው፡ በፍጹም አይቻልም። መንፈሳዊዉም ኾነ ሥጋዊው፡ ማለትም፡ መልአካዊውም ኾነ፡ ሰብአዊው ፍጡር፡ ባለቤት ያልኾነበትን ፍጡርነቱን፥ ወይም፡ ፍጥረትን፡ "እኔ፡ በባለቤትነት፡ መያዝና መግዛት አለብኝ! ወይም፡ ይገባኛል!" ሊል፡ ከቶ አይቻለውም።

እውነታውና ፍትሕ ርትዑ ይህ ከኾነ፡ ይህች መለኮታዊት መንግሥት፡ የተመሠረተችበትና የተቋቋመችበት፥ አገልግሎቷን የምትመራበትና ፍጥረቷን የምታስተዳደርበት፥ በህልውናዋ የምትቀጥልበትና ፍጡሯን የምታኖርበትም፡ የራሷ የኾነ፡ ሕያው ሥርዓታዊ አቋም ያላት መኾኗ፡ ሊታወቅ ይገባል። ይህን ሥርዓታዊ አቋም፡ "ምሁራን ነን!" የሚሉት፥ ወይም፡ በእነርሱ የሚመሩት፡ ዓለማውያን፡ "ሕገ መንግሥት"፥ ወይም፡ "ሕገ ሃይማኖት" እያሉ፡ በክርታስ ላይ ጽፈውና በመጻሕፍት መዝግበው፡ ሲመጻደቁበት ተኖሯል፤ ዛሬም፡ ይኸው፡ እየታየ ነው።

"ሲመጻደቁበት" የተባለው፡ እንዲያው በከንቱ፥ ወይም፡ በምፀት አይደለም፤ በአግባቡ ነው፤ እኒህ ሰዎች፡ እንኳንስ፡ አቃልለውና ነቅፈው የተዉትን፡ እውነተኛውን፡ የእግዚአብሔሩን ቀርቶ፡ ራሳቸው፡ ያወጡትን፥ የደነገጉትንም፡ ያንኑ የሓሰቱንም "ሕገ መንግሥት"፥ ወይም፡ "ሕገ ሃይማኖት" ቢኾን፡ በትክክልና በቅንነት፡ በሥራ ላይ አለማዋላቸው፥ ሊፈጽሙትም፡ ፍላጎቱም፥ ዕቅዱም፡ ጥንቱኑ የሌላቸው በመኾኑ ነው፤ እንዲያውም፡ ቀድሞውንም ተጠብበውና ተጠንቅቀው፥ ዐልመውም የደነገጉት፡ ራሳቸው ሊፈጽሙት ሳይኾን፡ ሌሎችን፡ የዋሃኑን፥ ብዙኃኑን ወገናቸውን፡ በረቂቅ ብልሃት ጠፍረው ሊገዙበትና ሊበዘብዙበት ስለኾነ ነውና።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ "**ዲበ መንበረ ሙሴ ነበሩ፤ ጸሓፍት ወፈሪሳውያን፤ ኵሎ ዘመሀሩክሙ ግበሩ፤ ወዕቀቡ፤ ወበከመ ዘይገብሩሰ፡ ኢትግበሩ! እስመ ዘይሜህሩ፡ ኢይገብሩ። ወየዐሥሩ ጾረ ዐቢየ፥ ወክቡደ፤ ወያሰክምዎ ለሰብእ፡ ዲበ መትከፍቱ፤ ወለሊሆሙሰ፡ ኢይለክፍዎ በአጽባዕቶሙ ጥቀ። ወኵሎ ምግባሮሙ ዘይገብሩ፡ ለዐይነ ሰብእ ይገብሩ።**" ማለትም፡ "**ጻፎችና ፈሪሳውያን፡ በሙሴ የሥልጣን ወንበር ላይ ተቀምጠዋል፤ ያስተማሯችሁን ኹሉ አድርጉ! ጠብቁም! እንደሚሠሩት ግን፡ አትሥሩ! የሚያስተምሩትን፡ አይሠሩትምና።ታላቅና ከባድ ሸክም አስረው፡ ሰውን፡ በጫንቃው ላይ ያሸክሙታል፤ እነርሱ ግን፡ በጣታቸው ስንኳ አይነኩትም። የሚሠሩትን ሥራቸውን ኹሉ፡ ለሰው ይምሰል ይሠሩታል።**" ብሎ የተናገረባቸው፡ ስለእነዚህ ሰዎች መኾኑን፡ ማስተዋል የሚሣነው፡ ቅን ተመልካች አይኖርም። (ማቴ. ፳፫፥ ፪-፭።)

ሰዎች፡ በግል ኾነ በጋራ፥ በአገርና በዓለም ዓቀፍ ደረጃ፡ በዚህ ዓይነቱ ሕገ መንግሥታቸው፡ ሥጋውያኑንና መንፈሳውያኑን፥ ዓለማውያኑንና ሃይማኖታውያኑን ኹሉ የሚያካትተውን፡ "ማናቸውንም ዓይነት ድርጅትና ማኅበር፥ 'መንግሥት'፥ ወይም፡ 'ሃይማኖት' የሚባሉትን ጭምር፡ አቋቁመው ሲሠሩ የኖሩት፥ ዛሬም፡ ሲያደርጉ የሚታዩት፡ ከቶ ለምንድን ነው?" ለሚለው ጥያቄ፡ ሰሚ ባይኖርም፡ እውነተኛውን መልስ መስጠት ግድ ይኾናል። ይህም፡ "እነዚህ ኹሉ ተቋማት፡ የእነዚሁ ሰዎች፡ መሣሪያዎች ኾነው፡ ሰብአዊዉንና ሰይጣናዊዉን፡ የፍላጎት ተግባራቸውን ሊያካኺዱባቸው፥ ሊገለገሉባቸውና ሊጠቀሙባቸው እንጂ፡ በጎውን የእግዚአብሔርን ዓላማ ሊፈጽሙባቸው አይደለም።" የሚለው ነው።

ይህ እንዳልኾነማ፥ እንዲያውም፡ በገሃድ ሲካኼድ እንደሚታየው፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ለፍጥረቱ መልካም ህልውና፡ ያቆመችለትን የተቀደሰ ዓላማና ሥርዓት፡ ኾን ብለው ለማፍረስ የተቋቋሙና የሚሠሩ ለመኾናቸው፡ ይኸው፡ እስከአኹን በሚታወቀው፡ የዓለም እውነተኛ ዜና መዋዕልና በዚህ ዘመን እየኾነ በቀጠለው፡ የሰዎች ድርጊት፡ ተረጋግጦ አብቅቶለት የለምን? አዎን!።

ስለዚህ፡ በግለሰቦች ፍጹም እውነተኛ ፈቃደኛነትና እነርሱም፡ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ባላቸው ቀጥታ ግንኙነት ጸንታ ከኖረችው፡ **ከኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት** ውጪ፡ በምንም ዓይነት መልኩና ይዘቱ፡ "መንግሥት" ኾነ " ሃይማኖት" ተብሎ የሚቋቋመውና የሚካኼደው ጭምር፡ ማናቸውም ዓይነት ተቋም፥ ወይም ድርጅት፥ ወይም ማኅበር፡ ሥጋዊ ኾነ መንፈሳዊ፥ ዓለማዊ ኾነ ሃይማኖታዊ፡ የእነዚሁ፡ የክፉ ሰዎችና የሰይጣን ተገዢና መሣሪያ ከመኾን፡ በምንም ዓይነት ጥበባዊ ዘዴ ሊያመልጥ፡ ከቶ አይቻለውም። በዚህ ምክንያት፡ የሰዎች የኾነው ኹሉ፡ ምንጊዜም፡ ፍጻሜው፡ ጥፋትና ሞት ኾኖ ሲቀር፡ የእግዚአብሔር የኾነው ብቻ ግን፡ ዕድገቱ፡ ልማትና ሕይወት ኾኖ ይቀጥላል።

<u>ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ከእነዚሁ፡ ክፉ ሰዎችና ከሰይጣን መሠሪ ጥቃት፡ ተጠብቃና ነጻ ኾና ለመኖር የቻለችው፥ ወደፊትም፡ በዚሁ ጸንታ መቀጠል የምትችለው፡ መለኮታዊ አቋሟና ሥርዓቷ፡ ለእነርሱ ያልተመቸ፥ ረቂቅና መንፈሳዊ በመኾኑ ነው። አዎን! በዜጎቿ ልቦና ውስጥ የተመሠረተች ናትና።</u>

ታዲያ! የዓለሙ ሰዎች፡ ሥርዓታዊ አቋማቸውን፡ "ሕገ መንግሥት"፥ ወይም፡ "ሕገ ሃይማኖት" እያሉ፡ በክርታስ ላይ ጽፈውና በመጻሕፍት መዝግበው፥ በሓውልትም ላይ ሳይቀር ቀርጸው፡ የሚመጻደቁበት ከኾነ፡ ያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት የኾነው ሥርዓታዊ አቋም፡ ተጽፎ የሚነበበውና ተመዝግቦ የሚገኘው የት ሊኾን ነው?

<u>ያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ሥርዓታዊ አቋምማ፡ ተጽፎ የሚነበበውና ተመዝግቦ የሚገኘው፡ የዚችው መንግሥት፡ ሰብአውያን ዜጎች በኾኑት፡ በወንዱ እና በሴቷ፡ ነፍሳዊ ልቦናና ሥጋዊ አእምሮ፥ መንፈሳዊ ኅሊናም ላይ ነው።</u>

እኒሁ፡ የዚች መንግሥት፡ ዜጎቿ የኾኑት የቃል ኪዳን ልጆቿ፡ እየራሳቸው፡ የእግዚአብሔር ሕግ የኾነው፡ የዚሁ ሕያው ሥርዓታዊ አቋም፡ አሥራጺዎችና ፈጻሚዎች፥ ፈራጆችና አስፈጻሚዎች እንደመኾናቸው፡ ይኸው፡ ሕያው ሥርዓታዊ አቋም፡ በግንድነትና በቅርንጫፍነት ያስገኛቸው፡ የመለኮታዊቷ መንግሥት ህልዋን አካላት የኾኑት፡ የሦስቱ የአገልግሎት ቤቶች፡ ማለትም፡ የቤተ ሕዝቡ፥ የቤተ ምልክናውና የቤተ ክህነቱ፡ ሙሉ አባሎች ናቸው።

የአባልነታቸውም ደረጃ፡ በጾታ፡ መለያየትና መበላለጥ ሳይኖርበት፡ ለወንዶቹም፥ ለሴቶቹም፡ እኩል ነው። ኹሉም፡ ወንድማማችና እኅትማማች ናቸው። በመካከላቸው፡ ገዥና ተገዢ፥ አዛዥና ታዛዥ፥ የበላይና የበታች፡ ከቶ የለም። እያንዳንዱ እና እያንዳንዷ፡ ተግባራቸውንና ግዳጃቸውን፣ ኃላፊነታቸውንና ተጠሪነታቸውን አውቀው፡ በቅንነት ያገለግላሉ።

በእነዚህ፡ ኪዳናውያንና ኪዳናውያት አባልነት፡ ሕያዋን ኾነው፡ በተዋሕዶ የሚሠሩት፡ ሦስቱ ህልዋን አካላት፡ በእየራሳቸው ተለይተው ሲገለጹ፡- በእግዚአብሔር መልክ የተፈጠረውን፡ የሰውን አካልና ባሕርይ፡ በአዛዥነት ሥልጣን የምትመራውን፡ ነፍስን መስሎና አክሎ የሚሠራው፡ "ቤተ ሕዝብ" የተባለው፡ የሕግ አሥራጺነት አገልግሎትን የሚሰጠው ዘርፍ፡ <u>ቀዳሚ</u> ኾኖ ይመደባል፤ <u>ቀጥሎ፡</u> ግዙፉን ቁሳዊ አገልግሎት የሚያቀርበው ዘርፍ፡ የሰውነትን ሥጋዊ አካልና ባሕርይ መስሎና አክሎ፡ ግዳጁን ሊፈጽም፡ "ቤተ ምልክና" ተብሎ፡ በአማካይነት ይመደባል፤ <u>በመጨረሻም፡</u> ረቂቁን የአእምሮ አገልግሎት የሚያበረክተው፡ የፈራጁና የሕግ ተርጓሚው ዘርፍ፡ የመንፈስን አካልና ባሕርይ መስሎና አክሎ ሊሠራ፡ "ቤተ ክህነት" ተብሎ፡ መንግሥታዊውን አቋም ለድምድማት በማብቃት ይመደባል።

እያንዳንዱና እያንዳንዷ፡ የዚች የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጋ፡ ከአባት አብራክና ከእናት ማሕፀን ፅንሰት ጀምሮ፡ ከፈጣሪያቸው፡ በተፈጥሮ ከተቀዳጁት፡ መለኮታዊ መብታቸው የተነሣ፡ የእግዚአብሔር ልጅ፥ የእግዚአብሔር ካህንና የእግዚአብሔር ነጋሢ የመኾንን ክብርና ጸጋ ላስገኘላቸው ባለቤትነት፡ የበቁ ኾነው ይገኛሉ። ስለዚህም፡ "ሥዩመ እግዚአብሔር"፥ ወይም፡ "ሥይምተ እግዚአብሔር" በሚለው ስመ ንግሥና፡ "አጼ"፥ ወይም "አጼዪት" እስከሚያስሰኘው፡ እስከ መጨረሻው ማዕርግ በሚያደርሰው፡ ከዝቅተኛው እስከከፍተኛው ደረጃ ላለው፡ ለማንኛውም የአገልግሎት ቦታ፡ ሌላውንና ሌላዪቱን አባል፡ እጩ አድርገው ሊያቀርቡና ሊመርጡ፥ እየራሳቸውም፡ እጩ ኾነው ቀርበው፡ ሊመረጡ የተገቡ ይኾናሉ። ይህ ብቅዓታቸው፡ በመለኮታዊዋ እውነትና በመንፈስ ቅዱስ ጸጋ፡ ሕይወታቸውን ሙሉ በሚያካኺዱት፡ ፍጹም አምልኳቸው ምክንያት፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ የዘውድና የዙፋን ባለቤቶች ከኾኑት፡ ከካህኑ አባት ንጉሥ፡ ከኢየሱስ ክርስቶስና ከካህኒቷ እናት ንግሥት፡ ድንግል ማርያም ጋር ያላቸው፡ ቀጥታ ግንኙነት፡ የተጠበቀላቸውና የጸናላቸው ኾኖ ይቀጥላል።

አንድ ሰው፡ ወንድ ኾነ ሴት፡ የዚች የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጋ ለመኾን፡ እንደሥጋውያኑና እንደመንፈሳውያኑ፥ እንደዓለማውያኑና እንደሃይማኖታውያኑ ልማድና ሥርዓት፡ ወደባለሥልጣን፡ አማላጅ፥ ወይም ሽማግሌ ልኮ፥ ወይም ገጸ በረከት፥ ወይም፡ እጅ መንሻ ይዞ፥ ወይም፡ ማመልከቻ ጽፎ፥ ወይም፡ ቅጽ ሞልቶ፡ ያንንም፡ በአንድ ሌላ ደጋፊ፥ ወይም፡ ዋቢ አስጸድቆ፥ በጽሑፍ ኪዳኑም አረጋግጦ ማቅረብ፥ ከዚያም፡ ስሙና የሕይወት ታሪኩ፡ በመዝገብ ተመዝግቦ፡ መለያ ቍጥርን ማግኘት፥ ወይም፡ መታወቂያ ክርታስን መቀበል አያስፈልገውም። ለዚህ ኹሉ ግልጋሎት ኾነ ቍሳቍስ፡ ምንም ዓይነት የገንዘብ ወጪ፥ ወይም፡ በየጊዜው የሚደረግ፡ ወቅታዊ ክፍያ፥ ወይም፡ አስተዋጽኦ አይጠየቅም። አባልነትን፡ በሕጋዊ እውቅና ለማረጋገጥ የሚፈጸም፡ የተለየ የመግቢያ ሥነ ሥርዓትም እንኳ የለም።

መጥምቁ ዮሓንስ፡ በአዋጅ ነጋሪነቱ፡ "አንሰኬ አጠምቀክሙ በማይ፡ ለንስሓ፤ ወዘይመጽእ እምድኅሬየ፡ ውእቱ ይጸንዕ እምኔየ፣ ዘኢይደልወኒ እጹር አሣእኖ፣ ውእቱ፡ ያጠምቀክሙ፡ በመንፈስ ቅዱስ፥ ወበእሳት!" ማለትም፡ "እኔ፡ ለንስሓ፡ በውኃ አጠምቃችኋለሁ፤ ጫማውን ለመሸከም የማይገባኝ፡ ከእኔ በኋላ የሚመጣው እርሱ ግን፡ ከእኔ ይልቅ ይበረታል፤ እርሱ፡ በመንፈስ ቅዱስ፥ በእሳትም ያጠምቃችኋል!" ሲል ባስሰማው፡ የእግዚአብሔር ቃል መሠረት፣

ራሱ፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስም፡ ለደቀ መዛሙርቱ፡ "'ዮሓንስ፡ አጥመቀ በማይ፤ አንትሙሰ ትጠመቁ [ታጠምቁ] በመንፈስ ቅዱስ!' ...'ወዘንተ ብሂሎ፡ ነፍኀ ላዕሌሆሙ፤ ወይቤሎሙ፡ 'ንሥኡ መንፈሰ ቅዱሰ!'" ማለትም፡ "ዮሓንስ፡ በውኃ አጠመቀ፤ እናንተ ግን፡ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ [ታጠምቃላችሁ]! ...ይህንም ብሎ፡ እፍ አለባቸውና፡ 'መንፈስ ቅዱስን ተቀበሉ!' አላቸው።" ሲል በተናገረው የምሥራች ቃሉ መሠረት፡ የዚች የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጋ ለመኾን፡ ስለአባልነት፡ ለወንድ ኾነ፥ ለሴት የሚፈጸመው የመግቢያ ሥርዓት፡ በ"እውነትና በመንፈስ" አምልኮ ለቀረበ፡ ለማንኛውም ሰብአዊ ፍጡር፡ በማይታየው በመንፈስ ቅዱስ እሳት ተካኺዶ የሚከናወን ስለኾነ፡ በውኃ የሚደረገው የምሥጢረ ጥምቀት ሥርዓት እንኳ አያስፈልግም። (ማቴ. ፫፥ ፲፩። ዮሐ. ፳፥ ፳፪። የሐዋ. ፩፥ ፭።)

በዚህ ኹኔታ፡ ከእግዚአብሔር በተሰጣቸው የተፈጥሮ ጸጋ፡ የዚች የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ ዜጎች የመኾንን ክብር፡ ከልደታቸው ጀምረው አግኝተው፡ ያደጉባትና የኖሩባት፥ ዛሬም እየኖሩባት ያሉ፡ ጥቂቶች ወንዶችና ሴቶች፡ በዓለም ላይ፡ አልታጡም፤ እነርሱም፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ናቸው። ብዙዎች ግን፡ ምርጫቸው፡ የክፉው ወገን ኾኖ በመገኘቱ፡ ከዚህ ታላቅ መለኮታዊ ጸጋና በረከት ተለይተውና ርቀው ኖረዋል፤ ከዚህ የተነሣም፡ ለጥፋት ተዳርገዋል። ዛሬ ያሉትም መሰሎቻቸው፡ የሚጠብቃቸው ጽዋ፡ ይኸው እንደኾነ ይታመናል።

ይኹን እንጂ፡ እነዚህ፡ ወንድ እና ሴት ግለሰቦች፡ እየራሳቸውን፡ ከተመሳሳዩ ጥፋት አድነው፡ ለእየራሳቸው፡ የወደፊት፡ መልካም ሕይወትና የዘለዓለም ደኅንነት ሲሉ፡ ምንጊዜም፡ በእውነተኛ ንስሓ፡ ወደፈጣሪያቸው ተመልሰው፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጋ ለመኾን የሚፈልጉ ቢኾን፡ ይህን በጎ ፍላጎታቸውን፡ ለጣፋጩ ፍሬ ለማብቃት፡ በእየራሳቸው ፈቃድና በየግላቸው ውሳኔ፡ እንዲፈጽሙ የሚጠየቁት፡ አጭርና ቀላል የኾነ፡ አስፈላጊ የመቀበያና የመግቢያ ሥርዓት አለ፤ ይኸውም፡ እንዲህ ነው፡-

<u>**በቅድሚያ፡**</u> በዚህ አዋጅ፡ የመቅድም አርእስት ሥር የሠፈሩትን፡ "የሃይማኖት እና የቅዱሱን ኪዳን ምስክርነት፣ የእግዚአብሔር ምስጋና እና የድንግል ማርያም ሰላምታ" የተባሉትን ቅዱሳት ቃላት፡ በግልጽና በትክክል ማወቅና መረዳት፥ መቀበልና ማመን ነው።

<u>**ቀጥሎ፡**</u> ቅዱስ ቍርባንን፡ ማለትም፡ የኢየሱስ ክርስቶስን፡ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም መቀበል ነው።

ይህ የምሥጢረ ቍርባን ሥርዓት፡ በማናቸውም ቤተ ክርስቲያን፥ ወይም፡ ይህን የመሰለው፡ የተለመደ ድርጅት የማይገኝ፥ ወይም፡ የሌለ ቢኾን፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ የመጀመሪያውን ሥርዓተ ቅዳሴ፡ "እንግዳ" በተባለ፡ በአንድ ተራ ሰው መኖርያ ቤት ውስጥ እንደፈጸመ ኹሉ፡ ከዚህ በታች በተገለጸው መልክና ይዘት፡ በራስ መኖርያ ቤት፥ ወይም፡ እንደበዓለ ጥምቀት፡ በማናቸውም ተስማሚ ቦታ፥ በሜዳም እንኳ ቢኾን፡ በዳስና በድንኳን ማካኼድ ይቻላል።

ምናልባት፡ እነዚህ ኹሉ ማማረጫዎች ሊገኙ፥ ወይም እውን ሊኾኑ የማይቻል ቢኾን ግን፡ ግለሰቦቹ፡ ይህን የምሥጢረ ቍርባኑን ሥርዓት፡ "በእውነትና በመንፈስ" አምልኳቸው አማካይነት፡ በእየራሳቸው እንዳካኼዱት በመቍጠርና ይህንኑም፡ ለእየራሳቸው በሃይማኖት በማረጋገጥ የሚፈጽሙት ከኾነ፡ እንደምሥጢረ ጥምቀቱ ሥርዓት ኹሉ፡ ያን፡ መለኮታዊ ጸጋ ስለሚያስገኝላቸው፡ የኢየሱስ ክርስቶስን፡ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም፡ በመንፈስ ቅዱስ እንደተቀበሉ እንደሚቆጠርላቸው፡ ማመን ይገባቸዋል። (ሉቃ. ፳፪፥ ፯-፳።)

<u>**ከዚያ በማስከተል፡**</u> በቤተ ክርስቲያንም ኾነ በግል መኖርያ ቤት፥ ወይም፡ በማናቸውም አመቺ ቦታ በመገኘት፡ በግዙፉ ሥጋዊ ዓይን በማይታየው፡ በካህኑ ንጉሥ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ እና በካህኒቷ ንግሥት፡ ድንግል ማርያም መንፈሳዊ ዙፋን ፊት ቆመው፡ ከዚህ በታች፡ በአዋጁ ቃል መፈጽም ርእስ ሥር የሠፈረውን፡ ለቅዱሱ ኪዳን ያላቸውን፡ የታማኝነት ማረጋገጫ ቃላቸውን፡ በይፋ መስጠት ነው።

__በመጨረሻም፡__ እግዚአብሔር፡ ለኖኅና ለልጆቹ፡ የዘለዓለም ቃል ኪዳን ምልክት አድርጎ የሰጠውንና በሦስቱ ዐበይት የቀስተ ደመና ቀለማት፡ ማለትም፡ በአረንጓዴ፥ ብጫና ቀይ አማካይነት የሚታወቀውን፡ የኢትዮጵያዊነት መለያ የኾነውን፡ የሦስቱን ቀለማት የክር ማተብ፡ እየራሳቸው፡ በጸሎት ባርከው፡ በየአንገታቸው ላይ ማሠር ነው።

__ከዚህ በኋላ፡__ በመለኮታዊው ዙፋን ፊት በሚፈጽሙት የአምልኮ ስግደት፡ የአባልነት ማረጋገጫው ሥርዓት ያበቃል።

በዚህ ሥርዓት፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጎች የኾኑት፡ እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ እና እያንዳንዷ ኢትዮጵያዊት፡ መምህረ ንስሓ አያስፈልጋቸውም፤ እየራሳቸው፡ ካህንና ካህኒት ከመኾናቸው ጋር፡ ካህኑ ንጉሥ ኢየሱስ ክርስቶስ እና ካህኒቱ ንግሥት ድንግል ማርያም፡ የእነርሱ መምህራነ ንስሓዎቻቸው ናቸውና።

ቅዱስ ቍርባንንና ሥርዓተ ጥምቀትን፥ ሌሎቹንም፡ የሃይማኖታቸውን ሥርዓት ለማካኼድና ለመፈጸም የሚችሉበት፡ የተዘጋጀ ድርጅት ከታጣ፡ ካህንና የቤተ ክርስቲያን ሕንፃም አያስፈልጋቸውም፤ እየራሳቸው፡ ካህንና ካህኒት ከመኾናቸው ጋር፡ የእያንዳንዳቸው ሕያው ሰውነት፡ አማናዊው የእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ነውና።

አዎን! ይኸው፡ __ሕያው ሰውነታቸው፡__ አሥሩ ቃላት የተጻፉባቸውን፡ ኹለቱን የኪዳን ጽላት የያዘችው ታቦት የተቀመጠበትን፡ መለኮታዊውን መሠዊያ መንበር አማክሎ የሚገኝ በመኾኑ ነው፤ የዚህ ሕያው ሰውነታቸው ማደሪያ የኾነው፡ መኖሪያ ቤታቸውም፡ ራሱ፡ ቤተ ክርስቲያን፡ ማለትም፡ የክርስቲያን ቤት ነውና።

እያንዳንዱና እያንዳንዷ የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጋ፡ በባለቤትነት የያዙትና የሚያገኙት ገቢ፥ ለየግላቸውና ለቤተሰባቸው፥ ለሌላው ለማናቸውም ተገቢ ግዳጃቸው የሚከፍሉት ወጪ፥ በጠቅላላ፡ ገንዘባቸውና ንብረታቸው ኹሉ፥ ሰውነታቸው ጭምር፡ የራሱ፡ የእግዚአብሔርና የእርሱ ስጦታ መኾኑን፡ ከቅዱሱ ኪዳን የተነሣ ያምናሉ፤ ኹለንተናቸውና የእነርሱ የኾነው ኹሉ፡ መቶ በመቶ፡ በሙሉ፡ የእርሱ ስለኾነ፡ "አሥራት በኵራት" ብለው፡ በፈጣሪያቸውና በእነርሱ መካከል ከፋፍለው የሚደለድሉትና የሚመድቡት ድርሻ፡ ጨርሶ የለም።

ያገኙትን ኹሉ፡ "የእርሱ ነው!" ብለው፡ በክብርና በምስጋና እንደሚቀበሉት ኹሉ፡ ለእየራሳቸው ሳይቀር፡ የሚያወጡትንም ኹሉ ደግሞ፡ እንዲሁ፡ "ለእርሱ ነው!" ብለው፡ በጥንቃቄና በልግሥና ስለሚያደርጉት፤ እንዲሁም፡ በነፍስ፥ በሥጋና በመንፈስ፡ ለእያንዳንዳቸው የሚያስፈጋቸውን፥ ከዚያም በላይ ሊደረግላቸው የሚገባውን ኹሉ፡ ፈጣሪያቸው፡ አስቀድሞ አስቦ እንዳዘጋጀላቸው፥ እያዘጋጀላቸው እንዳለና ወደፊትም እንደሚያዘጋጅላቸው ስለሚታመኑ፡ ምንም ዓይነት ችግር የለባቸውም።

*ፈጣሪያቸው እግዚአብሔር፡ የነፍሳቸውንና የሥጋቸውን፥ የመንፈሳቸውንም ደኅንነትና ጥበቃ በሚመለከት፡ በማናቸውም ኹኔታና አግጣጫ፡ በፍጹም ቅርበትና ትጋት እንደሚከታተል፡ በሃይማኖት ስለሚያውቁ፡ ስለአካል ጉዳትና ስለሕመም፥ ስለድንገተኛ አደጋና ስላልታሰበ የማጣት ችግር፥ ምንም ዓይነት ሥጋትና ጭንቀት የለባቸውም፤ ከእነዚህ ጠንቆች ብቻ ሳይኾን፥ የክፋት መንፈሳውያንና ሥጋውያን ተፃራሪዎቻቸው ከኾኑ ኃይላት ጥቃትም ኹሉ ጭምር፥ "የተፈጥሮ" ከሚባሉት መቅሠፍታት ሳይቀር፡ ፈጽመው ነጻ እንደኾኑ ተማምነው ይኖራሉ።*

ከዚህ የተነሣ፡ "የሕይወትና የጤና፥ የአደጋና የድህነት [ደሀ ላለመኾን] ዋስትና" የሚባለውን የመድን ውለታን፡ ከሥጋውያንና ከዓለማውያን የሰዎች ድርጅቶች ጋር መዋዋልን አይሹትም። ከእየራሳቸው ሃይማኖታዊና ምግባራዊ እውቀትና ጥንቃቄ ጋር፡ የቅዱሳን መላእክት፡ የማያቋርጥ ጥበቃ እንደማይለያቸው ስለሚያረጋግጡ፡ የመከላከያ ጦር ኃይል መሣሪያንና የሠራዊት ድርጅቱን አይፈልጉትም። እያንዳንዱና ኹሉም፡ የፍላጎትና የችግር ዓይነት፡ የቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖታቸው ባስገኘላቸው፡ የእውነትና የመንፈስ አምልኳቸው፡ በመንፈስ ቅዱስ መፍትሔ እንዲያገኝ ተደርጎላቸዋልና።

እያንዳንዱና እያንዳንዷ የእግዚአብሔር መንግሥት ዜጋ፡ ለዚች መንግሥት እንዲያበረክቱ የሚጠየቁት ድርሻ፡ እንደዓለማውያኑ፡ በየጊዜው፡ መገናኘትና መሰባሰብ እንኳ ሳያስፈልጋቸው፡ እየራሳቸው፡ በፈቃዳቸውና በምርጫቸው፡ በሠለጠኑበትና በየተጠሩበት ሙያቸው፡ በያሉበት ኾነው፡ በግልና በኅብረት፡ የየበኩላቸውን አገልግሎት፡ በቅንነትና በትጋት፥ በታማኝነትና በፍቅር እያካኼዱ ማከናወን ብቻ ነው። <u>ይህ፡ የእየራሳቸውም ኾነ፡ ተቀጥረው የሚያካኺዱት ሥራ፡ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ፡ ለፈጣሪያቸውና ለቅድስት እናቱ፥ ለእየራሳቸውና ለተፈጥሮ ወገናቸው እንዲያቀርቡት የተጠሩበት፡ ክህነታዊ አገልግሎታቸው እንደኾነ ያምኑበታል።</u>

## ኢትዮጵያዊው ማነው? ኢትዮጵያዊቷ ማናት?

እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ እና እያንዳንዷ ኢትዮጵያዊት፡ ሰባቱን መለኮታውያን ቃል ኪዳናት አጠቃልሎ በያዘው፡ በቅዱሱ ኪዳን ተዋሕዶ ሃይማኖታቸውና ምግባራቸው ጸንተው በሚኖሩበት ጊዜ፡ የህልውና ሕይወታቸው፡ **"በእግዚአብሔር መልክ ተፈጠሩ! 'ከእኛም፡ እንደአንዱ ኾኑ!'"** ላስሰኛቸው፡ ለሥላሴ፡ የአንድነትና የሦስትነት አርአያነት ምሥጢር በቀቶ ይገኛል፤ ይህ ብቅዓት እውን የኾነው፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ፡ በነፍስ፥ በሥጋና በመንፈስ አካላትና ባሕርያት ከተሠራው፡ ከአንዱ የሰብአዊነታቸው ተፈጥሮ የተነሣ ብቻ አይደለም።

ነገር ግን፡ ፩ኛ፡ የሴምን፥ የካምንና የያፌትን የዘር ሓረጎች፥ ፪ኛ፡ የእግዚአብሔርን ልጅነት፥ የክህነትንና የነጋሢነትን የጸጋ ክብር፥ ፫ኛ፡ የቤተ ሕዝብ፥ የቤተ ምልክናና የቤተ ክህነት አባልነትን ሥልጣናዊ መብት አዋሕዶ ያቀዳጃቸው በመኾኑ ጭምር ነው እንጂ።

አዎን! ቅድስት ድንግል ማርያምና መለኮታዊው የትስብእት ልጇ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ የኢትዮጵያዊነት፡ ፍጹማን መገለጫዎች ናቸው። በዓለም ውስጥ የሚገኝ፡ ሰብኣዊ የኾነ፡ ማናቸውም ወንድ፡ በዘሩ፥ ወይም በቀለሙ፥ ወይም፡ በማንነቱ ረገድ፡ የየትኛውም ወገን ቢኾን፡ ሰባቱን መለኮታውያን ቃል ኪዳናት አጠቃልሎ የያዘውን፡ ቅዱሱን ኪዳን ተቀብሎ የሚኖር ከኾነ፡ ለሙሉ አባልነት፥ ወይም፡ ዜግነት የበቃ ኢትዮጵያዊ ኾኖ ይቈጠራል። ሴቷም እንዲሁ፡ በዘሩዋ፥ ወይም በቀለሟ፥ ወይም፡ በማንነቷ ረገድ፡ የየትኛውም ወገን ብትኾን፡ ሰባቱን መለኮታውያን ቃል ኪዳናት አጠቃልሎ የያዘውን፡ ቅዱሱን ኪዳን ተቀብላ የምትኖር ከኾነች፡ ለሙሉ አባልነት፥ ወይም፡ ዜግነት፡ የበቃች ኢትዮጵያዊት ኾና ትቈጠራለች።

እኒህ ኢትዮጵያዊውና ኢትዮጵያዊቷ፥ በዚህም ረገድ፡ እነርሱን መስለው የሚገኙ፡ ሌሎች ግለሰቦች፡ በምድር ላይ ተሠራጭተው ቢኖሩ፡ እነዚህ ጭምር፡ የእግዚአብሔር ልጆች፥ የእግዚአብሔር ካህናትና ነጋሥያን የመኾንን ሉዓላዊ ክብር ይቀዳጃሉ፤ ይህም ማለት፡ እኒህ ሰዎች፡ በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖታቸውና ምግባራቸው ብቅዓት ምክንያት፡ የእነዚህ፡ የክብር ጸጋዎች ባለቤቶች ይኾኑና፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት የአገልግሎት ዘርፎች ውስጥ፡ የባለሙሉ ሥልጣን ሕዝባዊነት፥ ካህንነትና ምሉክነት ደረጃቸውን፡ በአባልነትና በዜግነት፥ በባለሚልነትና በባልደረብነት ሊያካኺዱ የሚችሉ ይኾናሉ።

እኒህ ግለሰቦች፡ ይህን የመሰለውን፡ ልዩና የመጨረሻ የኾነውን፡ የሥልጣንና የክብር መብት ሊያገኙ የበቁባቸው ምክንያቶች፡ ከዚህ ቀጥለው ተመልክተዋል፦

*የመጀመሪያው ምክንያት፡* **<u>በእግዚአብሔር መልክ መፈጠራቸው እና በእርሱው፡ በፈጣሪ ቃል፡ "ከእኛ እንደአንዱ ኾኑ!" የመባላቸው</u>** እውነታ የተመሠረተበት፡ አንደኛው፡ የአዳምና ሔዋን ቃል ኪዳን ነው።

በዚያ፡ በእግዚአብሔር አካላዊና ባሕርያዊ አንድነትና ሦስትነት ምሥጢር፡ የእያንዳንዱ ሰብኣዊ ፍጡር አቋም፡ እንዲሁ፡ ነፍስ፥ ሥጋና መንፈስ በተባሉት፡ በሦስቱ አካላትና ባሕርያት፡ ያን፡ የአንድነት ህልውናን አግኝቶ፡ ሕይወቱ በሕያውነት ስለሚቀጥል፡ ይህ እግዚአብሔራዊ እውነታ፡ ቀዳሚ ምስክር ኾኖ፡ ራሱ፡ በዚያ ሰውነት ውስጥ፡ የራሱን ምንነትና ማንነት፡ ለራሱና ለፍጥረተ ዓለሙ፥ ለፈጣሪውም፡ አጕልቶና አግዝፎ ይናገራል።

*ኹለተኛው ምክንያት፡* እግዚአብሔር፡ ከመልከ ጼዴቅ ጋር ያደረገው፡ ሦስተኛው ቃል ኪዳን ነው።

ለኢትዮጵያዊነት፡ ዋና አብነትና ለኢየሱስ ክርስቶስ ቀዳሚ አርአያነት፡ በገናንነት የታወቀው፡ ይህ፡ "መልከ ጼዴቅ" የተባለው ጻድቅ ሰው፡ ለቅዱሱ ኪዳን ካለው ፍጹም ታማኝነት የተነሣ፡ "የእግዚአብሔር ምእመን" ተብሎ፡ የቤተ ሕዝብነትን፥ "የልዑል እግዚአብሔር ካህን" ተብሎ፡ የቤተ ክህነትን፥ እና "የሳሌም ንጉሥ" ተብሎ፡ የቤተ ምልክናን ህልውና በማረጋገጡ፡ በእግዚአብሔር መንግሥት ውስጥ፡ ባለሚልነትን ያስገኘለት፡ ይህ መለኮታዊ ክብር፡ ተከታይ ምስክር ኾኖ ያስረዳል።

*ሦስተኛው ምክንያት፡* ከድንግል ማርያም በተወለደው፡ በእግዚአብሔር ልጅ በኢየሱስ ክርስቶስ በተገኘው ቤዛነት፡ ቅዱሱ ኪዳን፡ ራሱ፡ ለፍጹሙ ጸጋ በቅቶ፡ ሰዎችን፡ ማለትም፡ ወንዶችንና ሴቶችን ደግሞ፡ ለዚሁ ጸጋ ሊያበቃ የቻለበት፡ ሰባተኛው ቃል ኪዳን፡ የመጨረሻው ምስክር ኾኖ፡ የምሥራች ቃሉን ያውጃል።

ይህ፡ የመጨረሻና ዘለዓለማዊ ቃል ኪዳን፡ ካስገኘው የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ የተነሣ፡ በዚህ አዋጅ መቅድም ውስጥ ሠፍረው በሚነበቡት ጸሎታት እንደተገለጸው፡ የሃይማኖታችንና የምግባራችን አጠቃላይ ቍም ነገር የኾነውን፡ "አንተ ውእቱ፡ ክርስቶስ፡ ወልደ እግዚአብሔር ሕያው!" ማለትም፡ "አንተ፡ ክርስቶስ፡ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ!" የሚለውን፡ የእምነት መግለጫ ቃል፡ በቅዱሱ ኪዳን ሃይማኖታቸው ጠብቀው ለመኖር በቍርጥ የወሰኑ መኾናቸውን፡ አንድ ወንድ እና አንዲት ሴት ግለሰቦች፡ በእምነት ምስክርነታቸው አረጋግጠው በሚሰጡበት ጊዜ፡ በሊቀ ሓዋርያት ቅዱስ ጴጥሮስና "ባኮስ" በተባለው፡ በኢትዮጵያዊው አቤሜሌክ (በአዲስ ኪዳኑ ኢትዮጵያዊ ዣንደረባ) ዘንድ የታየው፡ የሃይማኖትና የምግባር ትንግርትና አስደናቂ ለውጥ፡ በእርሱም፥ በእርሷም ላይ ተከናውኖ ይፈጸማል።

ይህንም እውነት፡ ከዚህ በታች የተመለከቱት ኹለት የቅዱሳት መጻሕፍት ጥቅሶች ያረጋግጣሉ፡-

፩) "ወበጺሖ እግዚእ ኢየሱስ፡ ብሔረ ቂሣርያ ዘፊልጶስ፡ ተስእሎሙ ለአርዳኢሁ፡ እንዘ ይብል፡ 'መነ ይብልዎ ሰብእ፡ ለወልደ እጓለ እመሕያው?' ወይቤልዎ፡ 'ቦ እለ ይብሉከ፡ ‹ዮሓንስሃ መጥምቀ!› ወካልአን ይብሉከ፡ ‹ኤልያስሃ!› ወመንፈቆሙ ይብሉከ፡ ‹ኤርምያስሃ! ወእመ አኮ፡ አሓዱ፡ እምነቢያት ቀደምት!› ወይቤሎሙ፡ 'አንትሙኬ፡ መነ ትብሉኒ?' ወአውሥአ፡ ስምዖን ጴጥሮስ፤ ወይቤ፡ 'አንተ ውእቱ፡ ክርስቶስ፡ ወልደ እግዚአብሔር ሕያው!'

"ወአውሥአ እግዚእ ኢየሱስ፤ ወይቤሎ፡ 'ብፁዕ አንተ፡ ስምዖን ወልደ ዮና! እስመ ኢከሠተ ለከ፡ ዘሥጋ ወደም፤ አላ አቡየ ዘበሰማያት። ወአንሰ እብለከ፡ ከመ አንተ ኰኵሕ፤ ወዲበ ዛቲ ኰኵሕ፡ አሓንጻ ለቤተ ክርስቲያንየ፤ ወአናቅጸ ሲኦል፡ ኢይኄይልዋ። ወእሁበከ፡ መራኁተ መንግሥተ ሰማያት፤ ወዘአሰርከ በምድር፡ ይከውን እሱረ በሰማያት፤ ወዘፈታሕከ በምድር፡ ይከውን ፍቱሓ በሰማያት።"

ማለትም፡ "ጌታችን ኢየሱስም፡ የፊልጶስ አገር ወደምትኾን፡ ወደቂሣርያ ከተማ በደረሰ ጊዜ፡ ደቀ መዛሙርቱን፡ 'ሰዎች፡ የሰውን ልጅ [እኔን] ማን ይሉታል?' ብሎ ጠየቃቸው። እነርሱም፡ ‹'ዮሓንስ መጥምቅ ነህ!' የሚሉህ አሉ፤ ሌሎችም፡ 'ኤልያስ ነው!' ይሉሃል፤ እኩሎቹም፡ 'ኤርምያስ ነው!' ይሉሃል፤ ያም ባይኾን፡ 'ከቀደሙት ነቢያት፡ አንዱ ነው!' ይሉሃል፤› አሉት። እርሱም፡ 'እናንተስ ማን ትሉኛላችሁ?' አላቸው። ስምዖን ጴጥሮስም፡ መልሶ፡ 'አንተ፡ ክርስቶስ፡ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ!' አለው።

"ጌታችን ኢየሱስም መልሶ፡ እንዲህ አለው፡- 'አንተ! የዮና ልጅ ስምዖን! ይህን እውነት የገለጠልህ፡ የሰማዩ አባቴ መንፈስ እንጂ፡ ሥጋዊዉና ደማዊው አእምሮህ አይደለምና፡ ብፁዕ ነህ! አንተ፡ ዐለት እንደኾንህ፡ እኔ እነግርሃለሁ፤በዚያች ዐለት ላይም፡ ቤተ ክርስቲያኔን እሠራታለሁ፤ የሲኦል በሮችም፡ አይበረቱባትም። የመንግሥተ ሰማያትንም መክፈቻዎች እሰጥሃለሁ፤ በምድር ያሰርኸው፡ በሰማይ የታሰረ ይኾናል፤ በምድርም የፈታኸው፡ በሰማይ የተፈታ ይኾናል። (ማቴ. ፲፮፥ ፲፫-፳።)

፪) "ወእንዘ የሓውሩ፡ በጽሑ ኀበ ማይ፤ ወይቤሎ፡ ውእቱ [ኢትዮጵያዊ] ኅፅው፡ 'ነዋ ማይ! ወመኑ ይከልአኒ ተጠምቆ?' ወይቤሎ ፊልጶስ፣ 'ይደልወከ፡ ከመ ትእመን፡ በኵሉ ልቡናከ!' ወአውሥአ ውእቱ ኅፅው፤ ወይቤ፡- 'አነ አአምን፡ ከመ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ውእቱ፡ ወልዱ፡ ለእግዚአብሔር!' ወአዘዘ ያቅሙ ሠረገላሁ፤ ወአቀሙ፤ ወወረዱ ኅቡረ ኀበ ማይ፤ ፊልጶስ፥ ወውእቱ ኅፅው፤ ወአጥመቆ።"

ማለትም፡ "ሲኼዱም፡ ከውኃ ደረሱ፤ [ኢትዮጵያዊው] ዣንደረባም፡ 'ውኃ ይኸው! ታዲያ! መጠመቅን፡ ማን ይከለክለኛል?' አለው። ፊልጶስም፡ 'በፍጹም ልብህ፡ ልታምን ይገባሃል!' አለው። ዣንደረባውም መልሶ፡ 'ኢየሱስ ክርስቶስ፡ የእግዚአብሔር ልጅ እንደኾነ፡ እኔ አምናለሁ!' አለው። ሠረገላውንም፡ እንዲያቆሙ አዘዘ፤ ሠረገላውንም አቁመው፡ ፊልጶስና ዣንደረባው፡ በአንድነት፡ ወደውኃው ወረዱ፤ አጠመቀውም።" (የሓዋ. ፰፥ ፴፮-፴፰።)

በእግዚአብሔር እውነትና መንፈስ ኾነው፡ በዚህ መልክና ይዘት፡ "አንተ ውእቱ፡ ክርስቶስ፡ ወልደ እግዚአብሔር ሕያው!" ማለትም፡ "አንተ፡ ክርስቶስ፡ የሕያው እግዚአብሔር ልጅ ነህ!" የሚል፡ የእምነት ማረጋገጫ ቃልን የሚያሰሙት፡ እነዚህ፡ ኹለት፡ ወንድና ሴት ግለሰቦች፡ በቀጥታና በፍጹም ኹለንተናቸው፡ መልከ ጼዴቅንና ስምዖን ጴጥሮስን፥ ያን፡ 'አቤሜሌክ' የተባለውን ኢትዮጵያዊ ዣንደረባና እንዲያውም፡ ራሱን፡ ኢየሱስ ክርስቶስን የመምሰል ጸጋንና ክብርን ይቀዳጃሉ፤ እነዚህ፡ በስማቸው የተጠቀሱት ቅዱሳን፡ በመንፈስ ቅዱስ ያገኟቸው ሥልጣናትና ኃይላት ኹሉ፡ የእነርሱም ይኾናሉ። ይህንም እውነታ፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ የተናገራቸው፡ እንዲህ የሚሉት መለኮታውያት ቃላቱ፡ አረጋግጠው አጽንተውታል፡-

"አማን አማን እብለክሙ! ዘየአምን ብየ፡ ግብረ፡ ዘአነ እገብር፡ ውእቱኒ ይገብር፤ ወዘየዐቢ እምኔሁ ይገብር፤ እስመ አነ አሓውር ኀበ አብ። ወኵሎ ዘሰአልክሙ በስምየ፡ እገብር ለክሙ፣ ከመ ይሰባሕ አብ፡ በወልድ።" ማለትም፡ "እውነት እውነት እላችኋለሁ! በእኔ የሚያምን፡ እኔ የማደርገውን ሥራ፡ እርሱም ደግሞ ያደርገዋል፤ ከዚያም የሚበልጥ ያደርጋል፤ እኔ፡ ወደአብ እኼዳለሁና። አብ፡ በወልድ ይመሰገን ዘንድ፡ በስሜ የለመናችሁትን ኹሉ፡ አደርግላችኋለሁ።" (ዮሐ. ፲፬፥ ፲፪-፲፫።)

እነኚህ፡ ኹለት፡ ወንድና ሴት ግለሰቦች፡ እያንዳንዳቸው፡ በእየራሳቸው፡ ፈጣሪያቸው፡ በሰውነታቸው ውስጥ በተፈጥሮ ያቀዳጃቸውን፡ እግዚአብሔራዊ እውቀት ተገንዝበውትና ተቀብለውት፥ አምነውበትም የሚኖሩ መኾናቸውን፡ ለእየራሳቸው በሚያረጋግጡበት ጊዜ፡ የእያንዳንዳቸው፡ የዘር እና/ወይም የጐሣ፥ የማኅበራዊ እና/ወይም የሃይማኖት፥ የትምህርት እና/ወይም የሙያ አቋማቸው ምንነትና ማንነት ሳያግዳቸው፡ ለኢትዮጵያዊነት፥ ለኢትዮጵያዊትነት፣ ማለትም፡ በሥጋዊው፡ የአካል ፍጹም ነጻነትና በነፍሳዊው፡ የአእምሮ ፍጹም ነጻነት፥ በመንፈሳዊውም የህልውና ፍጹም ነጻነት ለሚገኝበት፡ ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ዜግነት ይበቃሉ።

አዎን! በዚያን ጊዜ፡ እነኚህ ግለሰቦች፡ የእግዚአብሔር ጸጋ የኾነውን ልጅነታቸውንና ካህንነታቸውን፥ ነጋሢነታቸውንም ባስገኘላቸው፡ በዚህ ኢትዮጵያዊነታቸው፡ እርስ በርስ መገናኘትና መሰባሰብ ሳያስፈልጋቸው፡ በየሚኖሩበት ቦታ ኾነው፡ ፈጣሪያቸው፡ በተፈጥሮ፥ እነርሱም፡ በገዛ ፍላጎታቸውና ምርጫቸው፡ በሥልጠና በተደራጁበት፡ የየግል ሙያቸው ተሠማርተው፡ የእግዚአብሔር መንግሥት የኾነችውን፡ ዓለማቸውን ኢትዮጵያን፡ በቅንነትና በትጋት፥ በትሕትናና በታማኝነት ያገለግላሉ።

## የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ፡ መገኛዋ፥ ማደሪያዋና መኖሪያዋ የት ነው?

የዚህ መጠይቃዊ ርእስ መልስ፡ እንደተለመደው፡ ቀላልና ግልጽ፥ ቀጥተኛና ግዙፍ በኾነው፡ በእግዚአብሔር እውነት፡ ገሃድ ኾኖ ይታወቃል፤ ይኸውም፡- **"የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ፡ መገኛዋ፥ ማደሪያዋና መኖሪያዋ፡ የእያንዳንዱ ሰብአዊ ፍጡር ሕያው አካል ነው!"** የሚል መኾኑን፡ እየራሱ ሰብአዊ ኅሊና ስለሚያስገነዝብ ነው።

እንግዴህ፡ ይህች መንግሥት፡ ሰፍና የምትገኝበት ቦታና ጊዜ፡ ያ ሰውነትና ህልውናው ብቻ ሳይኾን፡ ተግባሯንና አገልግሎቷን ጭምር የምታካኺደው፡ በዚያው ሰውነትና ህልውና ውስጥ መኾኑ፡ በዚህ እውነታ ይረጋገጣል። ስለዚህ፡ እነኚህ፡ ኹለት፡ ወንድና ሴት ግለሰቦች፡ እያንዳንዳቸው፡ በእየራሳቸው፡ የእውነትና የመንፈስ ቅዱስ አምልኳቸው አማካይነት፡ እርሷን ሲያውቋትና ሲቀበሏት፡ በዚያን ጊዜ፡ **እርሷ ራሷ፡ ራሷን፡ ትገልጥላቸዋለች፤ እነርሱም፡ ሕይወት አድርገዋት ይኖሯታል።**

ይኹን እንጂ፡ ምናልባት፡ እነርሱ፡ ይህችን መንግሥት፡ ንቀው ቢተውዋትና ከድተው ቢቃወሟትም እንኳ ቢኾን፡ **እርሷ፡ አትርቃቸውም፤** በሥጋዊው የድንቍርና ዐመድና በዓለማዊው የዕብሪት ተራራ፡ በውስጣቸው ተዳፍነው የቆዩትን፡ እነዚያን፡ የእግዚአብሔር እውቀትና እውነት፡ በመጨረሻው የንስሓ ትንግርታዊ ኃይል ገላልጠው እስኪያገኙ፥ ምርጫቸውም እርሷ በመኾኗ፡ ከሚያካኺዱት ገድል የተነሣ፡ የድላቸውን አክሊል እስኪቀዳጁ ድረስ፡ **በአጠገባቸው ቆይታ ትጠባበቃቸዋለች እንጂ፡ አትርቃቸውም።** የምርጫቸውና የገድላቸው ፍጻሜ፡ እርሷን በማወቅና በመቀበል ከተደመደመ፡ ለእነርሱ፡ "ኹሉ ነገር ተከናወነላቸው! አማረላቸው!" ማለት ነው። አለዚያ፡ እንዲህ ሳይኾንላቸው ቢቀር ግን፡ ዕድላቸውና ጽዋ ፋንታቸው፡ የዘለዓለሙ ጥፋት ይኾንባቸዋል።

ይህች፡ የእግዚአብሔር እውነት፡ ገዝፋ የታየችበትንና በአስተማማኝነት የተረጋገጠችበትን ኹኔታ፡ እንዲህ ከሚለው፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከተናገረው ቃል እናገኛለን፡- **"ወተስእልዎ ፈሪሳውያን፤ ወይቤልዎ፡- 'ማእዜ ትመጽእ መንግሥተ እግዚአብሔር?' ወአውሥአ፤ ወይቤሎሙ፡- 'ኢትመጽእ መንግሥተ እግዚአብሔር፡ በተዐቅቦ። ወይብልዋ፡ ‹ነያ ዝየ! ወነያ ከሓክ! መንግሥተ እግዚአብሔርሰ፡ ነያ ማእከሌክሙ ይእቲ።"**

ማለትም፡ **"ፈሪሳውያንም፡ 'የእግዚአብሔር መንግሥት፡ መቼ ትመጣለች?' ብለው ጠየቁት። እርሱም፡ መልሶ፡ እንዲህ አላቸው፡- 'የእግዚአብሔር መንግሥት፡ በመጠባበቅ አትመጣም። ‹እዚህ ናት! ወይም፡ እዚያ ናት!› አይሏትም፤ የእግዚአብሔር መንግሥትስ፡ እነኋት፡ በውስጣችሁ፣ በመካከላችሁ ናት!'"**
(ሉቃ. ፲፯፥ ፳-፳፩።)

## ኢትዮጵያዊነት ምንድን ነው?

በመደምደሚያው፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡** በጎዋ ሰሌዳዎቿና መድረኮቿ፡ በሌሎቹም፡ የመገናኛ መስመሮቿ አማካይነት፡ ለአንባብያን ባቀረበቻቸው፡ "ኢትዮጵያዊው፡ በማንነቱ ፍለጋ!"፥ "ኢትዮጵያ፡ የዓለሙ መፋረጃ!"፥ "ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት"፥ እንዲሁም፡ "ምሥራች! ከእናት ኢትዮጵያ! ለኢትዮጵያ ልጆች፤ ስለኢትዮጵያዊነት"፥ ደግሞም፡ "Ethiopia: The Classic Case"፥ በተባሉት መጻሕፍቷ ውስጥ፡ ስለዚህ፡ ታላቅ ርእሰ ነገር፡ ዝርዝር ሓተታ፡ በሚበቃ ተሰጥቶበታል። እዚህም ላይ፡ ከዚያ መጽሓፋዊ ማብራርያ የተውጣጣ፡ የተጨመቀ አጠቃላይ መግለጫ እንደሚከተለው ቀርቧል።

"ኢትዮጵያዊነት፡ ከዚህ የበለጠ፥ የመጠቀና የጠለቀ፥ የሰፋም ባሕርይ አለው፤ ይኸውም፡ ለኢትዮጵያ፥ እንዲሁም፡ ላለፉትና ለዛሬዎቹ፥ ለወደፊቶቹም ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ብቻ፡ ተለይቶና ተወስኖ የተሰጠ፥ እየተሰጠ ያለና የሚሰጥም አለመኾኑ ነው፤ ነገር ግን፡ በዘመነ ሓዲስ ኪዳን፡ ሞክሼው (መሰሉ) እንደኾነው፡ እንደክርስቲያንነት ኹሉ፡ የሰው ዘር፡ በመላ ተጠቃልሎ፡ በመለኮታዊቷ መንግሥት ሥር ተዋሕዶ፡ አንድ እንዲኾንበት፡ እግዚአብሔር አምላክ፡ ለፍጥረተ-ዓለሙ ደኅንነትና መልካም ሕይወት፡ አዘጋጅቶ የዘረጋው፡ ዘለዓለማዊ ዕቅድ ነው እንጂ። <u>ይህም፡ በምድር ላይ ላለው፡ ለሰው ልጆች ችግር ኹሉ፡ የመጨረሻው መፍትሔ እንደሚኾን ይታመናል።</u>

"ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡ በተከታታይ የተፈጸሙትን፡ እኒህን ቅዱሳት ኪዳናት፡ ከመጀመሪያው እስከመጨረሻው፡ ማለትም፡ ከአዳምና ሔዋን የፍጥረት ዘመን አንሥቶ፡ በዘመነ ሥጋዌ፡ እስከኢየሱስ ክርስቶስና ድንግል ማርያም መገለጥ ድረስ፡ ያልተቆጠበና ያልተገደበ፥ ወደር የሌለውንም መሥዋዕትነት በመክፈል፡ በሙሉ፡ ጠብቀዋቸው ኖረዋል።

"ኢየሱስ ክርስቶስ፡ የኢትዮጵያ አካላዊትና አማናዊት መገለጫ ከኾነችው፡ ከድንግል ማርያም፡ በሰውነት በተወለደ ጊዜ፡ እነዚህ ቅዱሳት ኪዳናት፡ በእርሱ ሥጋዌ፡ ፍጹም የኾነውን፡ አካላዊና አማናዊ ግዝፈትን መቀዳጀታቸው ታወቀ! በዚህም፡ ከእግዚአብሔር የተነገሩት፡ የትንቢት ቃላት ኹሉ፡ የመጨረሻውን ብቅዓት አግኝተው መፈጸማቸውና እግዚአብሔር፡ ለፍጥረቱ ያዘጋጀው፡ መለኮታዊ ዕቅድ፡ ከተወጠነለት ግብ መድረሱ ተረጋገጠ።

"ይህ፡ የኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያውያት ትውፊት፡ ከላይ እንደተወሳው፡ 'ሕያው ነው!' የተባለበት፡ ዓቢይና ልዩ ምክንያት አለው፤ ይኸውም፡ በቅዱሱ ኪዳን ውርስና ቅርስ ላይ የተመሠረተው፡ ኢትዮጵያዊው ትውፊት፡ ከትውልድ ወደትውልድ እየተላለፈ፡ ተጠብቆ የኖረው፡ እንዲያው፡ በተለመደውና ተራ በኾነው፡ በግዑዙ ቍሳቍስ ላይ በተቀረጸው ሰው-ሠራሽ ዘዴ አለመኾኑን፡ የሚያረጋግጠው እውነታ ነው። <u>በቅዱሱ ኪዳን ውርስና ቅርስ ላይ የተመሠረተው፡ ኢትዮጵያዊው ትውፊት፡ የተቀረጸውና ተጠብቆ የኖረው፡ በተለይ፡ ለመለኮት ዘለዓለማዊ ሥራ፡ ሕያው መገለጫው በኾነው፡ በኢትዮጵያዊው ሰውነት በመኾኑ ነው።</u>

"አዎን! በመጨረሻው ዘመን፡ የአዲሱ ኪዳን መሥዋዕት በኾነው፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም፡ ታድሶና ተጠናክሮ፡ ለዘለዓለማዊው ሕይወት የበቃው፡ ያ ኢትዮጵያዊ ሰውነት፡ ከአዳምና ሔዋን ጀምሮ፡ እስከዚህ፡ እስከዛሬው ጊዜ ድረስ ለቆየው፡ ፯ሺ፭፻፭ (ሰባት ሽህ አምስት መቶ አምስት) ዓመታትን ላስቆጠረው ዕድሜ፡ የእነዚህ፡ ሰባት ቅዱሳት ኪዳናት መለኮታዊ ማኅደር በመኾን አገልግሏል።

"እንኳንስ ቀደም ብሎ ይቅርና፡ በአኹኑ ጊዜም ቢኾን፡ እግዚአብሔር፡ ከሰው ዘር ጋር ላደረጋቸው ቃል ኪዳናት፡ ሕያው ምስክሩ፡ በእርግጥ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊው እና ኢትዮጵያዊቷ ብቻ ኾነው ይገኛሉ። ይህ እውነታ፡ በዐይነተኞቹ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ሕይወት ላይ፡ ገሃድ ኾኖ፡ ዛሬም ስለሚታይ፡ አማናዊነቱን ለማስተባበል፡ ከቶ አይቻልም።

"እንዲህ እንደመኾኑና ማናቸውም እውነተኛ ክርስቲያን፡ ሊኾን እንደሚገባው ኹሉ፡ 'የኢትዮጵያዊው ግለሰብ፡ የሰውነት አካል፡ የብሉዩንና የሓዲሱን ኪዳናት የያዙት፡ ቅዱሳት መጻሕፍት፡ ሥጋ ለብሰው፡ ሕያው የኾኑበት መዝገብ ነው!' ብለን አረጋግጠን እንናገራለን።

"ይህ፡ ለብፅዕና የሚያበቃ፡ የእግዚአብሔር ጸጋ፡ ከረዥም ዘመናት በፊት፡ በነቢዩ ኤርምያስ ትንቢታዊ አንደበት የተነገረው፡ ከዚህ የሚከተለው፡ አምላካዊ ቃል፡ ቀደም ብሎ፡ በበዓለ ሃምሳ ዕለት፡ መንፈስ ቅዱስን በተቀበሉት በሓዋርያትና ይኸው የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ፡ ወዲያው ተከታትሎ በወረደበት፡ በዚያ፡ 'የአዲስ ኪዳኑ አቤሜሌክ' በተባለው፡ ኢትዮጵያዊው ዣንደረባ ላይ ደርሶ የመፈጸሙን ምሥጢር ያበሥርልናል።

"ቃሉም፡ እንዲህ ይላል፡- «'ናሁ፡ መዋዕል ይመጽእ!' ይቤ እግዚአብሔር፤ 'ወእሠርዕ ለቤተ እስራኤል ወለቤተ ይሁዳ፡ ሥርዓተ ሓዲሰ። ወአኮ ከመ ዝንቱ ሥርዓት፡ ዘሠራዕኩ ለአበዊሆሙ፣ አመ አኀዝኩ በእደዊሆሙ፤ ወአመ አውጻእክዎሙ እምድረ ግብፅ፤ እስመ እሙንቱሂ ኢነበሩ በኪዳንየ፤ ወአነሂ ተሀየይክዎሙ፤' ይቤ እግዚአብሔር።

"«'ወከመዝ ይእቲ ሥርዓት፡ እንተ እሠርዕ ለቤተ እስራኤል፤ ወእምድኅረ እማንቱ መዋዕል፡ 'ይቤ እግዚአብሔር፡ 'እወዲ ሕግየ፡ ውስተ ልቦሙ፤ ወእጽሕፎ ውስተ ኅሊናሆሙ፤ ወእሬስዮሙ እንከ፤ ወእከውኖሙ አምላኮሙ፤ ወእሙንቱኒ፡ ይከውኑኒ ሕዝብየ።

"«'ወአልቦ ዘይሜህር እንከ፡ አሓዱ አሓዱ እኀዋሁ፤ ወአሓዱ አሓዱ ቢጾ፤ ወይብሎ፡ ‹አእምሮ ለእግዚአብሔር!› እስመ ኵሎሙ የአምሩኒ፣ ንኡሶሙ፥ ወዓቢዮሙ፤' ይቤ እግዚአብሔር፤ 'እስመ እሠሪ ሎሙ ኃጢአቶሙ፤ ወኢይዜከር እንከ አበሳሆሙ።'»"

"ማለትም፡ "«እግዚአብሔር አለ፡- 'እነሆ! ለእስራኤል ወገኖችና ለይሁዳ ወገኖች፡ አዲስ ሥርዓትን የምሠራበት ወራት ይመጣል!' እጃቸውን ይዤ፡ ከግብፅ አገር ባወጣኋቸው ጊዜ፡ ቀድሞ፡ ለአባቶቻቸው እንደሠራሁት፡ እንደዚያ ያለ ሥርዓት አይደለም፤ እነርሱ፡ በኪዳኔ አልጸኑምና፤ እኔም፡ ቸል አልኳቸው።' አለ እግዚአብሔር።

"«'ለእስራኤል ወገኖች የምሠራት ሥርዓት፡ እንዲህ ናት፤' አለ እግዚአብሔር። 'ከእነዚያ ወራት በኋላ፡ ሕጌን፡ በልቡናቸው አሳድራለሁ፤ በኅሊናቸውም እጽፈዋለሁ፤ እንግዴህ ወዲህም፡ እንዲጠብቁት አደርጋቸዋለሁ። እኔም፡ አምላካቸው እኾንላቸዋለሁ፤ እነርሱም፡ ሕዝቤ ይኾኑልኛል።'»"

"«'ከዚህ በኋላ፡ ‹እግዚአብሔርን እወቀው!› ብሎ፡ አንዱ፡ ለአንዱ፡ ወንድሙን፥ አንዱ፡ ለአንዱም፡ ባልንጀራውን የሚያስተምር የለም፤ ታናሹም፥ ታላቁም፥ ኹሉም፡ እኔን ያውቁኛል፤ ኃጢአታቸውን አስተሠርይላቸዋለሁና፤ በደላቸውንም፡ እንግዴህ ወዲህ አላስብባቸውምና።'»" (ኤር. ፴፩፥ ፴፩-፴፬።)

"እነዚህን የትንቢት ቃላት፡ ራሱ፡ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በትምህርቶቹ ውስጥ አውስቷቸዋል፤ ሐዋርያውም፡ ወደዕብራውያን በጻፈው መልእክቱ ውስጥ ጠቅሷቸዋል።

"በሰባቱ ቅዱሳት ኪዳናት ተመሥርታ የታነጸችው፡ መለኮታዊት መንግሥቱ፡ በእንዴት ያለ ኹኔታ፥ በምን ጊዜና በየትኛው ቦታ፡ በገሃድ ገዝፋ እንደምትሠራ፡ ብሩህና ቀጥተኛ በኾኑት፡ በእነዚህ ሕያዋን ቃላቱ፡ እግዚአብሔር፡ ፍጹም ግልጽ አድርጎ አሳይቷል።

"እግዚአብሔር፡ ለዚች መንግሥቱ አመሠራረትና አቋቋም፥ አመራርና አካኼድ፡ እጅግ የተራቀቁትና ውስብስብ የኾኑት፡ የሰው ልጆች፡ ድርጅታዊና ማኅበራዊ፥ ትምህርታዊና ንዋያዊ ሥርዓቶችና ጥበቦች፡ አላስፈለጉትም። አዎን! እነዚህ ኹሉ ነገሮች፡ ሰው፡ ራሱን በራሱ፡ በሙስና (በብልሹነት) እንዲደመስስ እስከማድረግ የሚያደርሱ፡ ሕፀፅን (ጕድለትን) እና ስሕተትን፥ ድክመትንና ስስትን የተመሉ ናቸውና፡ ለእግዚአብሔር አላስፈለጉትም።

"ዛሬ፡ በዚህ ቍሳዊ ዓለም ውስጥ፡ የመልካሚቱ ኑሮ ባለቤት ለመኾን፥ ወደፊትም፡ ለሚመጇት ፍጽምት ዓለም ለመብቃት ይችሉ ዘንድ፡ የሰውን ልጆች፡ ወደእውነትና ወደሕይወት ልዕልና የምታደርሰው መንገዱ፡ የምትመራበትን ዘለዓለማዊ መርሐ ግብርና የምትሰጠውን ጠቃሚ አገልግሎት፡ በሥራ ላይ ለማዋል፡ እግዚአብሔር፡ የሰብአዊ መንግሥትን አቋምና አሠራር አልመረጠም፤ ማለትም፡ ሕዝባዊ መመሪያን፥ ወይም፡ የሕግ አዋጅን፥ ወይም፡ የገንዘብ ድልድልንና ርስት ጕልትን፥ ወይም፡ የሠለጠነ የሰው ኃይልንና የትምህርት መሣሪያን፥ ወይም፡ መሠረታዊ የልማት አውታርንና ባለብዙ ዘርፍ የጽሕፈት ቤት ተቋምን፥ ወይም፡ አስገዳጅ የጦር ኃይል ያለውን፡ የሥራ አስፈጻሚ ባለሥልጣንን አልፈለገም፡ እግዚአብሔር። ሥራውን የሚያካኺደው በመንፈስ ስለኾነም፡ የእውነተኞቹ አገልጋዮቹ ግንኙነት እንኳ፡ በአካለ ሥጋ የጉባኤ ስብሰባ እንዲኾን አያስፈልገውም።

"ኹሉን ማድረግ የማይሣነው፡ እርሱ፡ ኃያሉ እግዚአብሔር፡ ዘለዓለማዊት የዘውድ መንግሥቱን፡ በምድር ላይ መሥርቶ ለማካኼድ ያስፈለገችው፡ አንዲት፡ ቅንጣት ነገር ብቻ ኾና ተገኘች! እርሷም፡ <u>ህልውናዋና አምልኮዋ፡ በእውነትና በመንፈስ ላይ የተመሠረተ፡ የዋህና ትሑት፥ ታማኝና ተነሳሒ የኾነች፡ ሰብኣዊት ልቦና ናት።</u>

"እግዚአብሔር፡ ያችን ልቦና ለማግኘት፡ ከዘመነ ፍጥረት አንሥቶ፡ በአዳምና ሔዋን፥ ከዚያም፡ በልጅ ልጆቻቸው ሰውነት፡ ፍለጋውን ጀመረ፤ እነሆም፡ በተለይ ለቃል ኪዳኑና ለአገልግሎቱ በበቁት፡ በኖኅና በሓይከል፥ በመልከ ጼዴቅና በሳሌም፥ በአብርሃምና በሣራ፥ በካህኑ ዮቶርና በብእሲተ ራጉኤል፥ በሙሴና በሲጳራ፥ በዳዊትና በቤትሳባ፥ በሰሎሞንና በማክዳ፥ ከዚያም፡ በኢያቄምና በሓና ተያይዛ እየወረደችና እየተጠበቀች ኖራ፡ በመጨረሻ፡ በአማናዊቷና በዳግማዊቷ ሔዋን፡ በድንግል ማርያም ሰውነት ውስጥ፡ ለፍጹምነት በቅታ አገኛት!

"በእርሷም ማሕፀን፡ እግዚአብሔር ቃል፡ 'አማናዊውና ዳግማዊው አዳም' ተብሎ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ የሥጋዌ አካል ተገለጸ! የዛሬው አዳም፡ ኢትዮጵያዊው እና የዛሬዋ ሔዋን ኢትዮጵያዊቷም፡ ቅዱሱን ኪዳን፡ ከኢየሱስ ክርስቶስ እና ከድንግል ማርያም፡ በመንፈስ ቅዱስ ተረክበው፡ ይኸው፡ እስካኹን፡ በባለአደራነት ጠብቀው፡ ለማቆየት የቻሉት፡ ከዚህ፡ ከቅዱሱ ኪዳን የጸጋና የበረከት ኃይል የተነሣ ነው።

<u>"አዎን! እግዚአብሔር፡ በትስብእት (መለኮት በተዋሐደው የሰውነት) ደም ታድሶ በጸናው፡ በቅዱሱ ኪዳን ሥርዓት የምትተዳደረውን፥ በልጁ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ክህነታዊ ንጉሥነትና በድንግል ማርያም ክህነታዊ ንግሥትነትም የምትመራውን፡ ዘለዓለማዊት የዘውድ መንግሥቱን፡ ህልውናዋ፡ በቀደሙት ተከታታይ የዘመነ ብሉይ ቃል ኪዳናት እየለመለመ በቀጠለባቸው፡ በእኒህ፡ በዛሬዎቹ ኢትዮጵያዊና ኢትዮጵያዊት፥ ሕያውና ሕያውት ዐለት ልቦና መሥርቶና አቋቁሞ፡ እነሆ፡ ሥራውን እያካኼደ ይገኛል። የዛሬው አዳም፡ ኢትዮጵያዊው እና የዛሬዋ ሔዋን ኢትዮጵያዊቷም፡ እናንተ ናችሁ።</u>

"ፈጣሪ፡ በቅዱሱ ኪዳን፡ ለፍጡሩ የሰው ዘር የሰጠው፥ ይህ፡ ወሰንና ወደር የሌለው፡ የተትረፈረፈ ጸጋ፡ ይህንኑ ኪዳን፡ እስከዛሬ አጽንተው ለጠበቁት፡ ለኢትዮጵያውያንና ለኢትዮጵያውያት ብቻ የታደለ ሳይኾን፡ በመላው ዓለም የሚኖሩ እውነተኞች ክርስቲያኖች ጭምር የሚጋሩት መኾኑ፡ እዚህ ላይ፡ በአንክሮ፡ ሊዘከር ይገባል።"

ቸሩ እግዚአብሔር፡ ዕፁብ ድንቅ አድርጎ፡ በመልኩ የሠራውና "ከእኛ፡ እንደአንዱ ኾነ!" ያስሰኘውን፡ የመጨረሻውን ሉዓላዊ ክብሩን ያቀዳጀው ሰብኣዊ ፍጡሩ፡ እንዲህ፡ በፍጹም ደስታና ወሰን በሌለው ምልዓት፡ እንዲኖረው ያዘጋጀለትና ያሰናዳለት ሕይወት፡ እነሆ እንግዴህ፡ ይህ ነው።

# መፈጽም።

ይህ አዋጅ፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡** በእግዚአብሔር እውነት፡ ለመላው የሰው ዘር በምታስተላልፈው፡ እንዲህ በሚለው፡ በዚህ፡ የመፈጽም መልእክት ቃል ይጠቃለላል፦

ዓለም ከተፈጠረበት ጊዜ ጀምሮ እስከዛሬ፡ የሰው ልጆች ምድራዊ ኑሮ፡ የምኞትና የስስት፥ የሲቃና የመቃተት፥ የሥቃይና የመከራ፥ የትንንቅና የዕልቂት እሳትና ማዕበል ያልተለየው፡ የቃጠሎና የድምሳሴ ሰለባ ኾኖ ቆይቷል። ይህም የኾነው፡ በሃይማኖቱና በፍልስፍናው፥ በዘር ማንነትና በቀለም ልዩነት፥ በማኅበራዊው ኑሮና በአገዛዙ ኹኔታ፥ በሥነ ብዕሉ፡ የገንዘብና የሀብት ድልድል፥ እንዲሁም፡ በትምህርት አሰጣጡና በሙያው አሰላለፍ ረገድ ያለው አስተሳሰብና አመራር፡ በማናቸውም መልኩና ይዘቱ፡ ከመሠረቱ፡ ከእግዚአብሔራዊው ሥርዓት፡ ፈጽሞ የተለየ፥ የተዛባና የተቃወሰ ከመኾኑ የተነሣ ነው።

እንዲህ ከኾነ፡ አኹን፡ ይህን የመሰለውን ተስፋ ቢስ አኗኗር፡ ከእነዚህ መሠረይ ጠንቆች አላቅቆና አንጽቶ፡ ነጻ በማድረግ፡ በእነዚህ ቦታ፡ እኩልነትንና ፍትሕን፥ መብትንና ደኅንነትን፥ ሰላምንና ብልጽግናን መተካት፡ እጅግ አስፈላጊ ኾኗል። ለዚህ እውነታ መልካም ፍሬያማነት፡ ሌላ ማማረጫ ከቶ አልተገኘም፤ አይገኝምም፤ የለምና። ለዓለሙ ሰዎች፡ ለችግራቸው ኹሉ፡ የመጨረሻው መልስና መደምደሚያው መፍትሔ ኾና ቀርባ ያለችው፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት** ብቻ ናት።

ስለዚህ፡ ይህን አዋጅ ያወጀችው፡ ይህችው፡ **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡** በአፍሪቃ፥ በእስያ፥ በኤውሮጳ፥ በመካከለኛውና በሩቁ ምሥራቅ፥ በሰሜኑ፥ በማእከላዊውና በደቡቡ አሜሪካ፥ በአውስትራልያ፥ በምሥራቃውያኑ እና በምዕራባውያኑ የውቅያኖሶቹ ደሴቶች ክፍላተ ዓለማት ኹሉ፡ ተያይዘውና ተከልለው የሚገኙት አገሮች ተወላጆች፥ ባላገሮችና ኗሪዎች ለኾናችሁት፡ ለእናንተ ወንዶችና ሴቶች፡ ለእያንዳንዳችሁ፡ በነፍስ ወከፍ፡ ይህን የግብዣ ጥሪዋን፡ እነሆ፡ በይፋ እያቀረበችላችሁ ናት።

እናንተም፡ "**አንትሙሰ፡ ኅሡ መቅድመ! መንግሥቶ፥ ወጽድቆ፤ ወዝንቱሰ ኵሉ፡ ይትዌሰከክሙ።**" ማለትም፡ "**እናንተ ግን፡ አስቀድማችሁ፡ የእግዚአብሔርን፡ መንግሥቱን፥ እውነቱን፡ ሹ! ይህም ኹሉ፡ ይጨመርላችኋል።**" ያለውን፡ የጌታችን የኢየሱስ ክርስቶስን፡ መለኮታዊ ቃል ተከትላችሁ፡ ይህች **ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት** ለቆመችለትና ለምታገለግለው፡ ለዚህ እውነትና እውቀት፥ እምነትና ሕይወት፡ እየራሳችሁን ልታበቁ፡ በቍርጥ የወሰናችሁ ከኾናችሁ፥ ይህንኑ ጥሪዋን ተቀብላችሁ ትፈጽሙታላችሁ። (ማቴ. ፮፥ ፴፫።)

ደግሞም፡ ህልውናችሁ፡ በወንድና በሴት ጾታዎች፡ የተፈጥሮ ኅብረትና እኩልነት ላይ ተመሥርቶና ጸንቶ፡ ከዚህ የደረሰው፥ ወደፊትም፡ በሚያስተማምን ኹኔታ እንዲህ ሊቀጥል የሚችለው፡ በዚሁ፡ **በእግዚአብሔር መንግሥትና እውነት ብቻ መኾኑን፡ የምታምኑ ከኾናችሁ፡** አዎን! በእርግጥ፡ ይህንኑ ጥሪዋን ተቀብላችሁ ትፈጽሙታላችሁ።

ፈጣሪ፡ እንደቃል ኪዳኑ፡ ለዚች፡ **ለኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥቱ፡** የወሰናት ቀን ደርሳ፡ በገሃድ እስከሚገልጣችሁና እስከሚያሰባሰባችሁ ድረስ፡ ይህንኑ ጥሪዋን ተቀብላችሁ የምትፈጽሙትም፡ እንዲህ ነው፡-

የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊ/ኢትዮጵያዊት የሚያስሰኘውን፡ የእግዚአብሔርን እውቀትና እውነት፡ በሚገባና በሚበቃ ከተረዳችሁ፥ ያንም ተቀብላችሁ ካመናችሁበት በኋላ፡ በእየራሳችሁ ነጻ ፈቃድና ምርጫ፡ በምትሰጡት ውሳኔ መሠረት፡ ከላይ የተሰጠውን መመሪያ ተከትላችሁ፡ ለዚያ ጸጋና ክብር የሚያበቃውን፡ ቅዱስ ቍርባንን፡ እሱም፡ የኢየሱስ ክርስቶስን ሥጋና ደም የመቀበሉን ሥርዓት ትፈጽማላችሁ።

ያን እንደፈጸማችሁ፡ አስቀድማችሁ፡ ከዚህ በታች የሠፈረውን፡ ቅጽ፡ ለእየራሳችሁ ምንባብና መዘክር እንዲኾናችሁ ትሞላላችሁ፤ እሱም፡ጽሑፍ ኪዳናችሁን የምታሠፍሩበት ሰነድ አይደለም፤ ዋናውን፥ ወይም፡ ቅጂውን የምትልኩለት መሥሪያ ቤት፥ ወይም፡ ጽሕፈት ቤትም የለም። በእየግላችሁ ማኅደር የምታስቀሩትና ለየራሳችሁ ማስታወሻ የምታስቀምጡት ነው።

ይኸው ቅጽ፡ ሌላ ሓተታ የሌለው፡ ዓለማዊዉንና ሰማያዊዉን ሙሉ ስሞቻችሁን፥ እንዲሁም፡ የሥጋ ልደትና የመንፈስ ጥምቀት ቀኖቻችሁን፥ ደግሞም፡ ይህን ሥርዓት የምትፈጽሙበትን ዕለት የያዘ ነው። ከዚያ ቀጥላችሁ፡ በሞላችሁት ቅጽ ላይ የሠፈረውን፡ የምስክርነት ቃላችሁን፡ በያላችሁበት፡ ለቃል ኪዳን ፈጣሪያችሁና ለቅድስት እናቱ፡ ቆማችሁ፡ በንባብ እያሰማችሁ ትሰጣላችሁ!

በዚህ አጭርና ቀላል፥ ቀልጣፋና ግልጽ ሥርዓት፡ **<u>የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ፡ ዘለዓለማውያን ዜጎች ትኾናላችሁ። በዚህም ዜግነታችሁ፡ በእግዚአብሔር፡ የሕይወት መጽሓፍ ውስጥ፡ በመንፈስ ቅዱስ ጸሓፊነት፡ ስማችሁ፡ በሕያውነት ይመዘገብላችኋል፤ ከዚህ የተነሣ፡ በዚህ ምድራዊ ዓለም ሳይቀር፡ በሥጋ፥ በነፍስና በመንፈስ፡ መልካሙን የገነት ሕይወት መኖር ትጀምራላችሁ።</u>**

በዓለማውያኑ ሰዎች ዘንድ የተለመደውን፡ ክርክርና ትግል፥ መካሰስና ጭቅጭቅ፥ አቤቱታና ሰልፍ፥ ጠብና ጦርነት ማካኼድ፥ እንዲያውም፡ እርስ በርሳችሁ መገናኘትና በጉባኤ መሰብሰብ እንኳ ሳያስፈልጋችሁ፥ ጣፋጭና ቅን የኾነውን፥ ይህን፡ የደስታና የእርካታ ግዳጃችሁን፡ ያለአንዳች ድካምና ውጣውረድ፡ እንዲህ፡ በየግላችሁና በያላችሁበት፡ በእርጋታና በጨዋነት፥ በሰላምና በፍቅር፥ በጸጥታና በሥርዓት በመፈጸማችሁ፡ የክፋትን ኃይላት፡ እኩይ ዓላማና መሠሪ ዕቅድ፡ ታከሽፉታላችሁ።

ይህንም፡ በሓሰትና በግፍ፥ በክህደትና በዓመፅ፥ በጥላቻና በጦርነት የተመላ፥ የተጐሣቈለ ዓለም፡ ከሙስናው (ከብልሹነቱ) አንጽታችሁ፡ ለእየራሳችሁና ለፍጥረተ ዓለሙ ኹሉ፡ የፍጹሙ ሕይወት መኖሪያ ልታደርጉት ይቻላችኋል።

ሥጋውያን ሰዎች፡ 'መንፈሳውያን ነን!' ከሚሉ አስመሳዮች ተባባሪዎቻቸው ጋር በመመሣጠር፡ በየአገራቸው ክልል፡ የእግዚአብሔር ሃይማኖቱና ሥልጣኑ ቀርቶ፡ የስሙ አጠራር እንኳ፡ ደብዛው፡ በአቋማቸውና በሕጋቸው ውስጥ፡ በምንም መልኩና ይዘቱ፡ ጨርሶ እንዳይወሳና እንዳይገኝ በማድረግ፡ እየራሳቸውን፡ 'መንግሥት' እያሉ፡ ወገናቸውን መግዛታቸው ሳይበቃቸው፥ በየክፍለ ዓለማቸውም፡ የበይነ-አህጉራት ማኅበራትን አቋቊመው መደጋገፋቸው ሳያንስ፡ "አንድ፡ የዓለም መንግሥትን ልንፈጥር፡ እየሠራን ነን!" በሚል፡ የሽፋን ዕቅድ ተሰባስበው፡ የሚሸነጋገሉበትና የሚገባበዙበት፡ "የተባበሩት የዓለም መንግሥታት ማኅበር" የሚሉት ድርጅታቸው፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ፡ በእነርሱ ዘንድ፡ ፈጽማ እንደሌለች መቈጠሯን መስክሮባቸዋል።

አዎን! በመላው ፍጥረተ-ዓለም፡ እስካኹን፡ በኅቡዕ (በረቂቁ መንፈስ ቅዱስ) ሰፍና የኖረችውና አኹንም ያለችው፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ ዛሬ፡ ራሷን ገሃድ አድርጋ፡ በዚህ አዋጅ፡ ለምድር ወገኖች ኹሉ ስለገለጠች፡ በዚህ፡ በእያንዳንዳችሁ፡ የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ተዋሕዶ ሃይማኖታችሁና ምግባራችሁ ተሳትፎ፡ እንግዴህ፡ የእርሷን ማንነትና ምንነት አጕልቶ የሚያሳየውን፡ ተአምራዊና ትንግርታዊ ደጋግ ኹኔታዎች፡ ለመመልከትና ለማግኘት እንደምትችሉ፡ ይህችው፡ ኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት፡ "እውነት በእውነት!" እያለች ታረጋግጥላችኋለች።

ለቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነት ያላችሁን፡ የታማኝነቱን የምስክር ቃል የመስጠቱን ሥርዓት እንደፈጸማችሁ፡ ለዚህ ታላቅ የሕይወት ጸጋና ክብር በመብቃታችሁ ደስ ብሏችሁ፡ ይህን ኹሉ ላደረጉላችሁ፥ ለዚህም ፍጹም ጸጋና ታላቅ ክብር ላበቋችሁ አምላክና ለእናቱ፡ በዚህ አዋጅ መቅድም ሥር የሠፍሩትን የምስጋናና የሰላምታ ገጸ በረከቶች፡ በየዕለቱ ጸሎታችሁ እንደምታቀርቡላቸው፡ እሙን ነው።

በመጨረሻ፡ ፈጣሪያችሁ፡ ጥንቱኑ አዘጋጅቶላችሁ፥ እናንተ ግን፡ በገዛ ፈቃዳችሁና ምርጫችሁ፡ "አንፈልገውም!" ብላችሁ፡ ትታችሁት ቆይታችሁ፡ አኹን፡ በእውነተኛ ንስሓ ለተመለሳችሁበት፡ ለዚህ፡ ለፍጹሙ ሕይወት በመብቃታችሁ፡ በዚህ አዋጅ ግርጌ የሠፈሩትን መዝሙሮች፡ በደስታና በሓሤት መንፈስ ኾናችሁ፡ በዘወትሩ የምስጋና ቍርባናችሁ ላይ እንደምትዘምሯቸውም፡ እርግጥ ነው።

ቸሩ እግዚአብሔር፡ ዕፁብ ድንቅ አድርጎ፡ በመልኩ የሠራውና "ከእኛ፡ እንደአንዱ ኾነ!" ያስሰኘውን፡ የመጨረሻውን ሉዓላዊ ክብሩን ያቀዳጀው ሰብኣዊ ፍጡሩ፡ ቀድሞም አስውቦና አሟልቶ በፈጠራት፥ ኋላም፡ በትስብእት ደሙ አጥቦና አንጽቶ ባደሳት፡ በዚች ምድራዊት ገነት፡ እንዲህ፡ በፍጹም ደስታና ወሰን በሌለው ጸጋ፡ እንዲኖረው ያዘጋጀለትና ያሰናዳለት፡ መልካሙ ሕይወት፡ እነሆ ይህ ነውና፡እንግዴህ፡ ለእየራሳችሁ እወቁበት። እውን አድርጉት። ኑሩት።

# <u>ቃለ አሚኖት ዘኢትዮጵያዊ/ት</u>



| | |
|---|---|
| ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ<br>ኢየሱስ ክርስቶስ<br>ካህኑ ለዓለም፡ በከመ ሢመቱ ለመልከ ጼዴቅ ኢትዮጵያዊ<br><u>ንጉሠ ጽዮን፥ ወንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ</u> | ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር<br>ድንግል ማርያም<br>እሙ ለአምላክነ፥ ወእምነ ዘዚአነ<br><u>ንግሥተ ጽዮን፥ ወንግሥተ ነገሥታት ዘኢትዮጵያ</u> |
| The Conquering Lion of the Tribe of Judah<br>Jesus Christ<br>Eternal Priest in the Order of Melche-Zedeq the Ethiopian<br>King of Zion and King of Kings of Ethiopia | Ethiopia stretches out Her Hands to God<br>The Virgin Mary<br>Mother of God and Our Holy Mother<br>Queen of Zion and Ethiopia |

---

አነ_________________________________፥ ወስምየ ዘክርስትና _____________________________፥ ወልደትየ ዘኮነ በወርኃ__________፥ በ____ዕለት፥__________ዓ. ም. በሀገረ ___________________________፤ ዮም፡ በዝ ወርኃ__________፥ በ____ዕለት፥__________ዓ. ም. እቀውም፡ በቅድመ መንበሮሙ ለኢየሱስ ክርስቶስ ወለድንግል ማርያም፡ በአምልኮተ ጽድቅ ዘመንፈስ ቅዱስ፡ ወናሁ አሰምዕ ስምዕየ በአጽንዖት፣ እንዘ እብል፡–

“አነ ውእቱ ኢትዮጵያዊ/ት ዘኪዳን ቅዱስ፡ ዘእሄሉ፡ በዐቂበ ርትዕት ሃይማኖትየ፡ ጽሪት፡ በምሥጢረ ተዋሕዶ፡ እንተ ተመሥረት፡ በዝንቱ ኪዳን ቅዱስ፡ ዘውእቱ መዝገቦሙ ለሰብዓቱ ኪዳናት፡ ዘተካየዶን እግዚአብሔር ምስለ ሰብእ፣ እላንቱ፡ ዘተወጥና በአዳም ወሔዋን፥ ወተሓደሳ በሰብእናሆሙ ለኖኅ፥ ወለመልከ ጼዴቅ፥ ወለአብርሃም፥ ወለሙሴ፥ ወለዳዊት፡ እስከልደተ ኢየሱስ ክርስቶስ እምድንግል ማርያም፡ ዘተፈጸማ በዛቲ ትስብእት፥ ወዘተግህደት በምግባርየ፥ ወዓዲ ዘእሄሉ በአንጽሖተ ርእስየ፡ በንስሓ፥ ወበአጽድቆተ ሰብእናየ፡ በተመጥዎተ ሥጋሁ ቅዱሰ ወደሞ ክቡረ።

“ኦ አምላኪየ ወመድኃኒየ፥ ካህንየ ወንጉሥየ ኢየሱስ ክርስቶስ! እሰግድ በቅድመ መንበርከ ወእሴብሓከ፡ እስመ አብቍዐተኒ ከመ በክሡት አሰምዕ፡ ዝ ስምዕ፡ በተአምኖትየ ዘቃልከ መለኮታዊት፡ ዘትብል፡ ‘ኵሉ ዘየአምን ብየ፡ በቅድመ ሰብእ፡ አነሂ አአምኖ፡ በቅድመ አቡየ ዘበሰማያት፤ ወዘሰ ክሕደኒ በቅድመ ሰብእ፡ አነሂ እክሕዶ፡ በቅድመ አቡየ ዘበሰማያት።’” (ማቴ. ፲፥ ፴፪-፴፫።)

“ኦ ቅድስት ድንግል ማርያም፥ ሃይማኖትየ ወሀገርየ፥ እምየ ወንግሥትየ እምኀበ ኢየሱስ ክርስቶስ! አበርክ ቅድመ መንበርኪ ወአቀርብ ለኪ፡ አምኃየ ዘስባሔ፡ በቃለ ገብርኤል መልአክ ቅዱስ፡ እስመ በፍቅርኪ ወበረድኤትኪ፡ ኮንክኒ ማሕፀንትየ፡ ከመ እጽናዕ በኢትዮጵያውናየ ዘቅዱስ ኪዳን፡ በኵሉ መዋዕልየ። ለዓለመ ዓለም፤ አሜን።”

# የኢትዮጵያዊ/ት፡ የታማኝነት ማረጋገጫ ቃል

| | |
|---|---|
| ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ | ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር |
| ኢየሱስ ክርስቶስ | ድንግል ማርያም |
| ካህኑ ለዓለም፡ በከመ ሢመቱ ለመልከ ጼዴቅ ኢትዮጵያዊ | እሙ ለአምላክነ፥ ወእምነ ዘዚአነ |
| ንጉሠ ጽዮን፥ ወንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ | ንግሥተ ጽዮን፥ ወንግሥተ ነገሥታት ዘኢትዮጵያ |
| The Conquering Lion of the Tribe of Judah | Ethiopia stretches out Her Hands to God |
| Jesus Christ | The Virgin Mary |
| Eternal Priest in the Order of Melche-Zedeq the Ethiopian | Mother of God and Our Holy Mother |
| King of Zion and King of Kings of Ethiopia | Queen of Zion and Ethiopia |

---

እኔ፡ ______________________________፥በክርስትና ስሜ___________________________ የተባልሁ፥ በ_______________ቀን፥__________ዓ. ም. በ __________________________________የተወለድሁ፤ ዛሬ፡ በዚህ______________ቀን፥__________ ዓ. ም. በኢየሱስ ክርስቶስ እና በድንግል ማርያም መንበር ፊት፡ በእውነተኛው፡ የመንፈስ ቅዱስ አምልኮ ቆሜ፡ እንዲህ እያልሁ፡ የምስክርነት ቃሌን በማረጋገጥ እሰጣለሁ።

“እኔ፡ በኢትዮጵያውያን የሃይማኖትና የቃል ኪዳን ጸሎቶች ውስጥ እንደተገለጸው፡ በአዳምና ሔዋን ተጀምሮ፡ በኖኅ፥ በመልከ ጼዴቅ፥ በአብርሃም፥ በሙሴና በዳዊት በኩል እየታደሰ፡ እስከኢየሱስ ክርስቶስ እና ድንግል ማርያም ደርሶ በተፈጸመው፥ በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የተደረጉትን፡ ሰባቱን ኪዳናት በአጠቃለለው፡ በቅዱሱ ኪዳን ተመሥርታ የቆመችውን፥ በምሥጢረ ተዋሕዶ የጠራችውንና የቀናችውን ሃይማኖቴን ጠብቄና በምግባር አጽንቼ፡ ራሴን፡ በንስሓና በሥጋ ወደሙ እያጸደቅሁ የምኖር፡ **የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊ/ኢትዮጵያዊት ነኝ።**

“አምላኬና መድኃኒቴ፥ ካህኔና ንጉሤ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ! "**በሰው ፊት፡ በእኔ አምኖ ለሚመሰክርልኝ ኹሉ፡ እኔ ደግሞ በሰማያት በአለው አባቴ ፊት፡ ስለታማኝነቱ እመሰክርለታለሁ። በሰው ፊት የሚክደኝንም፡ እኔ ደግሞ፡ በሰማያት በአለው አባቴ ፊት፡ ስለክህደቱ እመሰክርበታለሁ።**" ያልኸውን መለኮታዊ ቃልህን አምኜ፡ በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነቴ፡ ይህን የምስክርነት ቃል፡ በይፋ እንድሰጥ ስላበቃኸኝ፡ በመንበርህ ፊት እየሰገድሁ አመሰግንሃለሁ። (ማቴ. ፲፥ ፴፪-፴፫።)

"በኢየሱስ ክርስቶስ፡ ሃይማኖቴና አገሬ፥ እናቴና ንግሥቴ፡ ቅድስት ድንግል ማርያም ሆይ! በቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያዊነቴ ጸንቼ እኖር ዘንድ፡ በፍቅርሽና በረድኤትሽ ስላልተለየሽኝ፡ በመልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ቃል፡ በመንበርሽ ፊት ወድቄ፡ የምስጋና ሰላምታዬን አቀርብልሻለሁ። ለዘለዓለሙ፤ አሜን።

\+ \+ \+

## የኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያውያት፡
## የቅዱሱ ኪዳን መዝሙር።

ሃሌ ሉያ ለአብ፡ ለሰማይ አባታችን፤
ስብሓት ለእግዚአብሔር ወልድ፡ ካህን ንጉሣችን፤
ለመንፈስ ቅዱስም፡ ጸጋ ሕይወታችን፤
አቅርበናልና፡ በዝርጉ እጃችን፤
ጌታ ሆይ! ተቀበል፡ ይኸው ምስጋናችን።

ሰላም ለማርያም፡ ጽዮን እናታችን፤
ኪዳነ ምሕረት፡ ድንግል ንግሥታችን፤
ተዋሕዶ ሃይማኖት፡ ቤተ ክርስቲያናችን፤
ርስትሽ ነንና፡ በሕዝብነታችን፤
ይሰማ በአርያም፡ ይኸ መዝሙራችን።

ለሰውነታችን፡ ለመንፈስ ምግባችን፤
ለሕመም መድኃኒት፡ ለደዌ ፈውሳችን፤
ከክፋት፥ ከኃጢአት፥ ከሞት መዳኛችን፤
በመከራ ጊዜ፡ ተስፋ መጽናኛችን፤
በእምነትና ምግባር፡ የትእግሥት ፍሬአችን።

ለግል፥ ለቤተሰብ፥ ለኅብረት ኑሮአችን፤
ለአንድነት፥ ለፍቅር፥ ለሰላም ግባችን፤
ለሰብአዊ መብት፥ ለፍትሕ ዋስትናችን፤
አጥቂ እንዳይጎዳን፡ አለኝታ ጋሻችን፤
ለድል አድራጊነት፡ መሣሪያ ኃይላችን።

ለዚህ ፊደላችን፡ ለግእዝ ቋንቋችን፤
ለእውቀት፥ ለጥበብ፥ ለሥልጣኔአችን፤
ለልማት፥ ለዕድገት፥ መሠረት ሕንፃችን፤
በተፈጥሮ ውበት፡ ገነት አገራችን፤
የምንኖርበት፡ የታሪክ ክብራችን፤

ለኖኅ ልጆች ውሕደት፡ የዘር ሓረጋችን፤
ለኢትዮጵያዊነት፡ መጠሪያ ስማችን፤
ለማንነታችን፡ ልዩ ማስረጃችን፤
በቀስተ ደመና፡ ነጻነት ልብሳችን፤
የማርያም መቀነት፡ ሰንደቅ ዓላማችን።

አንበሳው ክርስቶስ፡ ምልክት አርማችን፤
ካምላክ ያገኘነው፡ ሕገ መንግሥታችን፤
ማንም የማይነጥቀን፡ የሰማይ ወርቃችን፤
የምንጠብቀው፡ ያደራ ውርሳችን፤
ቅዱሱ ኪዳን ነው፡ ሕያዉ ቅርሳችን።

## የኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያውያት፡
## የመከራ ጊዜ መዝሙር።

ኢትዮጵያ ሆይ! ሀገራችን! ረስቼሽ እንደኾን፡ ቀኜ ትርሳኝ!
ያላሰብሁሽ እንደኾን፡ መላሴ፡ ትናጋዬን፡ ሰልቶ ይውጋኝ፤
ከደስታዬ ኹሉ በላይ፡ ኢትዮጵያ ሆይ! አንቺ ባትኾኚ ስደት ይብላኝ።
አቤቱ! ፈጣሪያችን! በኢትዮጵያ ቀን፡ ጠላቶቿን ኹሉ አስብ፤
አፍርሷት፡ ኢትዮጵያን፡ እስከመሠረቷ ድረስ፡ የሚሉትንም ሕዝብ።
እናንት ትምክህተኞች፡ የኢትዮጵያ ፀሮች! የተንኰላችሁን ብድራት፤
የሚመልስ ነው፡ አምላካችን፣ በፍትሕ፥ በተአምራት፤
በሚጠሉሽ ላይ፡ በእውነት፣
በቅን፡ ለሚፈርደው ንጉሥ፡ ምስጋናችን ይብዛለት።
ኢትዮጵያ ሆይ! ሀገራችን! ረስቼሽ እንደኾን፡ ቀኜ ትርሳኝ።

## የኢትዮጵያውያንና የኢትዮጵያውያት፡
## የሰንደቅ ዓላማ መዝሙር።

ኢትዮጵያ፡ *(ድንግል ማርያም)* ሆይ! ደስ ይበልሽ!
በአምላክሽ ኃይል፡ በንጉሥሽ *(በኢየሱስ ክርስቶስ)*።
ተባብረዋልና ልጆችሽ *(የቅዱሱ ኪዳን ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት)*፤
አይነካም ከቶ ነጻነትሽ።
ብርቱ ናቸውና ተራሮችሽ፤ *(ቅዱሳንሽና ቅዱሳትሽ)*
አትፈሪም ከጠላቶችሽ።
የድል ሰንደቅ ዓላማችን፤
ይኑርልን ለክብራችን።

## ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡
## ለእግዚአብሔር የሚያቀርቡት ምስጋና፡ በመዝሙር።

አባታችን ሆይ! የምትኖር በሰማይ፤
መንግሥትህ በስምህ፡ ሰፈነች በእኛ ላይ።
በሰማይ የጸናች ሕያው ፈቃድህ፤
ተፈጸመች በምድር፡ በሥግው ቃልህ።
ፍቅርህ ለምግባችን፡ ፍጥረትን የሰጠች፤
በደልን ደምስሳ፡ ዕርቅን መሠረተች፤
ጌታ ሆይ! አዳንኸን፡ ከሞት፥ ከፈተና፤
በልጅህ ቤዛነት፡ በትንሣኤው ፋና።
ኃይልና ምስጋና፡ ጸንተው ለመንግሥትህ፤
አበቃኸን እኛን፡ ለቅዱስ ኪዳንህ።

## ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት፡
## ለድንግል ማርያም የሚያቀርቡት ሰላምታ፡ በመዝሙር።

እናታችን ሆይ! ማርያም ድንግል፤
ሰላም ለአንቺ ይኹን! በገብርኤል ቃል፥ በመልአኩ ቃል።
በሥጋ አካልሽ፡ ደግሞም በኅሊና፤
ባሕርይሽ ኾነ፡ ፍጹም ድንግልና።
ላሸናፊው አምላክ፡ ለእግዚአብሔር እናት፥ ለጌታ እናት፤
ማቅረብ ይገባናል፡ ሰላምታን በምንት፥ ሰላምታን በውነት፤
ከሴቶች መካከል፡ ባለሽ ቅድስና፤
ማሕፀንሽ አፈራ፡ የሕይወትን መና።
ደስ ይበልሽ አንቺ፡ የእግዜር ባለጸጋ፥ የአምላክ ባለጸጋ፤
አቅርቢን ከልጅሽ፡ ደሙ ኾኖን ዋጋ።

\+ + +

ተዐውደ፡ በነሓሴ ፲፮ ቀን፥ ፩፱፩፫ ዓመተ ምሕረት፡ ታወጀ።
በበዓለ ትንሣኤሃ፡ ለቅድስት ድንግል ማርያም ወላዲተ አምላክ።

ላእከ ኢትዮጵያ፡ ዘመንግሥተ እግዚአብሔር፣
የእግዚአብሔር መንግሥት ኢትዮጵያ አገልጋይ፣
ንቡረ እድ ኤርምያስ ከበደ ወልደ-ኢየሱስ፤
ስመ ጥምቀቱ፡ ኂሩተ-ወልድ።